www.abyssinialaw.com

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፳፪
አዲስ አበባ ግንቦት ፰ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No.22
ADDIS ABABA, 16th May, 2024

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፬/፪ሺ፲፮
በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች አዋጅ.....ገጽ ፲፭ሺ፫፻፷፯

Content

Proclamation No. 1314/2024
Federal Government -Owned Enterprise
Proclamation .....Page 15367

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፬/፪ሺ፲፮
በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች ላይ የሚደረግ የአሠራር ውጤታማነታቸውንና የፋይናንስ አቋማቸውን ለማጠናከር የሚያስችላቸውን እርምጃዎች መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች ከግል ድርጅቶች ጋር በግልፅ ውድድር መሥራት የሚችሉበትን አቅም ለማጠናከርና ምርታማነታቸውንና ትርፋማነታቸውን ለመጨመር ለንግድ ቅልጥፍና ያላቸውን አመለካከት የሚቀይር አመቺ የሆነ የቁጥጥር ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

PROCLAMATION No 1314/2024
Federal Government -Owned Enterprise Proclamation

WHEREAS, the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia aims to take necessary measures for the reorientation of State-owned enterprises towards operational and commercial efficiency;

WHEREAS, it has become necessary to create a conducive environment to enable State-owned enterprises to operate in open competition with private enterprises and to create a conducive regulatory environment thereby increasing their productivity and profitability;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

www.abyssinialaw.com

በመንግሥት ባለቤትት የተያዙ የልማት ድርጅቶች አሠራራቸውን ለማሻሻል የሚያግዝ የቁጥጥርና አጠቃላይ የክትትል ሥርዓቶችን በመዘርጋት የመንግሥትን የባለቤትነት መብት አጠቃቀምን ማጠናከር እና በእነርሱም ላይ የሚደረገውን አጠቃላይ ቁጥጥር ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, there is a need to strengthen the exercise of Government ownership right of public resources and improve the oversight of State-owned enterprises by establishing systems of supervision and oversight that will enable them to improve their performance;

በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች ተጠያቂነታቸውን በማረጋገጥና ግልፅነትን በማዳበር ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበትን ሥርዓት በመዘርጋት የኮርፖሬት አስተዳደራቸውን ከዓለም ዐቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎች ጋር ማጣጣሙ ጠቀሜታው የላቀ በመሆኑ፤

WHEREAS, it is imperative to align the corporate governance of State-owned enterprises with international best practices by establishing the autonomy of their management while holding them accountable and enhancing their transparency;

በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሕዝብ አገልግሎት ግዴታቸውን በሚወጡበት ጊዜ ተገቢ ያልሆነ የአሠራርና የፋይናንስ ጫና ሳይኖርባቸው ሥራቸውን ማከናወን የሚያስችላቸውን ግልፅ ዓላማና የፋይናንስ ስርዓት ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, when State-owned enterprises perform a public service obligation, it has become essential to set a clear objective, financing strategy and monitoring system to achieve their obligation without causing undue burden to the operation and finance of the State-owned enterprises;

በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶችን የፋይናንስ አፈፃፀማቸውን ማሻሻል እና የፊስካል ስጋትንና በመንግሥት ፋይናንስ ላይ የሚያሳድሩትን ጫና መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, it has become necessary to improve the financial performance of State-owned enterprises and minimize fiscal risk and the burden to public finances;

በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሚሠሩበትን የሕግ ማዕቀፍን ማዋሃድና ማሻሻል ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትና ብሔራዊ ሀብት አስተዋጽዎ ለማድረግ የሚኖራቸውን አቅም የሚፈጠር መሆኑ ግንዛቤ በመወሰዱ፤

WHEREAS it is acknowledged that improving the regulatory framework under which State-owned enterprises operate would help to unlock their potential in contributing to socio-economic development, and national wealth;

በኢትዮጵያ ፌደራሊዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

www.abyssinialaw.com

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፬/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩/ **"በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት"** ማለት፡-

(ሀ) በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ወይም የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ማቋቋሚያ ሕግ መሠረት የተቋቋመ ሙሉ ለሙሉ ወይም አብላጫው ድርሻ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት፤

(ለ) የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር በወጣው አዋጅ መሠረት ከመንግሥት ሙሉ ባለቤትነት ወደ አክሲዮን ማኅበርነት የተለወጠ የልማት ድርጅት፤

(ሐ) መንግሥት አነስተኛ ድምፅ ኖሮት ወርቃማ አክሲዮን የያዘበት ወይም ውጤታማ ቁጥጥር የሚያደርግበት የልማት ድርጅት፤

ነው፡፡

፪/ **"ወርቃማ አክሲዮን"** ማለት የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ስለማዛወር በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺/፪ሺ፲፪ መሠረት የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን በመለወጥ የካፒታሉ አካል የሆነና በማናቸውም የቦርድ ውሳኔ ላይ ድምፅ የመስጠትና ድምፅን በድምፅ የመሻር

PART ONE

GENERAL

1/ Short Title

This Proclamation may be cited as the "Federal Government-Owned Enterprises Proclamation No.1314/2024".

2/ Definitions

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "**State-Owned Enterprise**" means any of the following:

a) a wholly or majority Government-owned business organization established pursuant to a regulation of the Council of Ministers or the establishing law of a State holding company;

b) a business organization formed by the conversion of a wholly State-owned enterprise into a share company pursuant to the Privatization Proclamation;

c) a business organization in which the State holds a golden share or exercises effective control while holding minority share in an enterprise.

2/ "**Golden Share**" means a share in the capital of a company, formed by conversion of a public enterprise pursuant to the Privatization Proclamation No. 1206/2020, carrying such special rights as are set out in the Articles of Association of the company

www.abyssinialaw.com

መብቶችን ለመንግሥት የሚያስናፅፍ በአክሲዮን መመስረቻ ፅሁፍ ውስጥ የተደነገጉ ልዩ መብቶችን ያያዘ አክሲዮን ነው፡፡

to enable the Government to protect national interest with voting and veto rights over any board resolution.

፫/ **"ውጤታማ ቁጥጥር"** ማለት በባለቤትነት ከተያዙ አክሲዮኖች ከሚመነጭ ድምፅ የመስጠት መብት፣ ለባለአደራ በተላለፈ መብት ወይም በስምምነት ወይም በሌላ መንገድ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘን የልማት ድርጅት አስተዳደር እና ፖሊሲዎችን የመምራት ወይም እንዲመራ የማድረግ ሥልጣን ነው፡፡

3/ "**Effective Control**" means the possession, directly or indirectly, of the power to direct or cause the direction of the management and policies of a state-owned enterprise, whether through the ownership of voting stock, the use of a voting trust, contractual arrangements, or other wise.

፬/ **"ሚኒስቴር"** ማለት የገንዘብ ሚኒስቴር ነው፡፡

4/ "**Ministry**" means the Ministry of Finance.

፭/ **"ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን"** ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሠረት በመንግሥት ባለቤትነት በተያዙ የልማት ድርጅቶች ውስጥ የመንግሥትን የባለቤትነት መብቶች በበላይነት እንዲቆጣጠር ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት ተቋም ነው፡፡

5/ "**Supervising Authority**" means an institution of the Government mandated to oversee the ownership rights of the State in State-owned enterprises established by a regulation of the Council of Ministers.

፮/ **"የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ"** ማለት ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል በመንግሥት የተያዘን የንግድ ድርጅት በመንግሥት ስም በሥሩ ያደረገ፣ በባለቤትነት የሚያስተዳድር፣ የሚቆጣጠርና የክትትል ሥራ የሚያከናውን ሙሉ ለሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ነው፡፡

6/ "**State Holding Company**" means a wholly State-owned business entity established to hold, own, supervise and exercise control over State-owned enterprises and partially owned enterprises on behalf of the Government.

፯/ **"ጠቅላላ ሀብት"** ማለት ካለፉት ክንዋኔዎችና ከእነዚሁ የሚገኙ በመንግሥት ባለቤትነት ወደ ተያዘው የልማት ድርጅት ይመጣሉ ተብለው የሚጠበቁ የወደፊት ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ወይም እምቅ አገልግሎት ምክንያት በመንግሥት ባለቤትነት በተያዘ የልማት ድርጅት ቁጥጥር የሚደረግበት ሀብት ነው፡፡

7/ "**Total Assets**" means resources that are controlled by a State-owned enterprise as a result of past events and from which future economic benefits or service potential are expected to flow to the State-owned enterprise.

www.abyssinialaw.com

፲፯/ **"የተጣራ ሀብት"** ማለት ዕዳዎችን ሁሉ በመቀነስ የሚገኘው በመንግሥት ባለቤትነት በተያዘው የልማት ድርጅት ሀብት ውስጥ የሚገኝ ቀሪ የሆነ ጥቅም ነው።

፲፰/ **"ካፒታል"** ማለት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት በሚቋቋምበት ወቅት የሚመደብ የተጣራው ሀብት እሴት ነው።

፲፱/ **"የተጣራ ትርፍ"** ማለት የሥራ ማስኬጃ እና ከአጠቃላይ ገቢው ታክስን/ግብርን፣ ወለድና የእርጅና ተቀናሽን ጨምሮ ሌሎች ክፍያዎች ከተቀነሱ በኋላ የሚገኝ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ትርፍ ነው።

፳/ **"መንግሥት"** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራሊዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ነው።

፳፩/ **"ኦዲተር"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፳፱ መሰረት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘን የልማት ድርጅት ሂሣብ እንዲመረምር የተፈቀደለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

፳፪/ **"ሕጋዊ መጠባበቂያ ገንዘብ"** ማለት ኪሣራንና ዕዳን፣ የንብረት መጠበቂያን/መጠገኛን እና ኢንቨስትመንትን የመሳሰሉ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ ወደፊት ለሚያጋጥሙ ያልታሰቡ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚውል ከተጣራ ትርፍ በመቀነስ በመንግሥት ባለቤትነት በተያዘ የልማት ድርጅት በመጠባበቂያነት የሚያዝ ገንዘብ ነው።

፳፫/ **"የዳይሬክተሮች ቦርድ"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ መሠረት የተቋቋመ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ቦርድ ነው።

8/ **"Net Asset"** means the residual interest in the assets of the State-owned enterprise after deducting all its liabilities.

9/ "**Capital"** means the value of the net assets assigned to a State-owned enterprise at the time of its establishment or any time there after.

10/ "**Net Profits**" means the profit of a State-owned enterprise after operating expenses and all other charges including taxes, interest and depreciation have been deducted from total revenue.

11/ "**Government or state**" means the Federal Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

12/"**Auditor**" means a natural or juridical person who is authorized under Article 29 of this Proclamation to audit the accounts of a State-owned enterprise.

13/ "**Legal Reserve Fund**" means a fund maintained by a State-owned enterprise by deducting from its net profit to cover any unexpected future expenses including losses and liabilities, costs of upkeep, and to finance activities such as investments.

14/ "**Board of Directors**" means the board of a State-owned enterprise formed in accordance with Article 15 of this Proclamation.

www.abyssinialaw.com

፲፭/ "የሕዝብ አገልግሎት ግዴታ" ማለት በዚህ አዋጅ እና በመንግሥት ባለቤትነት በተያዘው የልማት ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ ወይም ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ለሕዝብ ለማቅረብ የተጣለበት ግዴታ ነው።

፲፮/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

፲፯/ በዚህ አዋጅ በወንድ ፆታ የተገለጸዉ የሴትንም ፆታ ያካትታል።

፲፰/ በዚህ አዋጅ አንድ ሕግ ወይም የሕግ ድንጋጌ ሲጠቀስ፣ የተጠቀሰውን ሕግ ወይም ድንጋጌ ሁሉንም ማሻሻያዎች ይጨምራል። ሕጉ ወይም ድንጋጌው በሌላ አዲስ ሕግ ወይም ድንጋጌ ከተተካም በዚህ አዋጅ የተመለከተው ማጣቀሻ፣ የተካውን ሕግ ወይም ድንጋጌ እንደሆነ ይቆጠራል።

፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በፌደራል መንግሥት ባለቤትነት በተያዙ የልማት ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት
የአዋጁ ዓላማዎች

፬. ዓላማዎች

ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

፩/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች በኢኮኖሚው ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ውጤታማነትን፣ አትራፊነትንና ተወዳዳሪነትን ግባቸው አድርገው ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ማድረግ፤

15/ "**Public Service Obligation**" means an obligation imposed on State-owned enterprise by this Proclamation and the establishment regulation of State-owned enterprise or a directive by the Ministry to provide goods or services for the benefit of the public.

16/ "**Person**" means any natural or legal person.

17/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

18/ Any reference in this proclamation to any other law or sections thereof shall include such law as amended or substituted and any regulations promulgated thereunder from time to time in effect.

3. Scope of Application

This Proclamation shall apply to all Federal Government owned enterprises.

PART TWO
OBJECTIVES OF THE PROCLAMATION

4. Objectives

This Proclamation shall have the following objectives:

1/ Require State-owned enterprises to operate with the goals of enhancing economic efficiency, profitability, and competitiveness in the economy;

www.abyssinialaw.com

፪/ በመንግሥት ባለቤትነት በተያዙ የልማት ድርጅቶች ላይ መንግሥት የሚያፈሰው ኢንቨስትመንት በኢንዱስትሪው ደረጃ በቂ ትርፍ እንዲያገኝ ማድረግ፤

2/ Provide the Government, as an owner, adequate return on its investment in State-owned enterprises in line with industry standards;

፫/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የተቋቋሙበትን ዓላማ መሠረት በማድረግ የሥራ አመራራቸውንና ለሕዝብ አገልግሎቶች የመስጠት ግዴታቸውን በውጤታማነትና በቅልጥፍና ማከናወናቸውን ማረጋገጥ፤

3/ Ensure that State-owned enterprises are effective and efficient in the management and delivery of their public services obligation in accordance with their establishment objective;

፬/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች በሚኒስቴሩ አማካኝነት በሚሰጥ የመንግሥት አቅጣጫ የሕዝብ አገልግሎት ግዴታቸውን ሲወጡ ግልፅነት የተላበሰ የወጪ እና የፋይናንስ ማዕቀፍ እና የክትትል ስርዓት በሥራ ላይ ያዋሉ መሆናቸውን እና በንግድ ላይ ያተኮረው ተልዕኮዋቸው ለድርድር ያልቀረቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

4/ Ensure that, when carrying out public service obligations at the direction of the Government through the Ministry, there is a clear costing for the public service obligation, financing framework and monitoring system in place and the commercial mandate of State- owned enterprises is not compromised;

፭/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች አስተዳደርና አመራር ኃላፊነት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት በተላበሰ መንገድ እየተከናወነ መሆኑን እና መልካም የኮርፖሬት አመራርና አስተዳደር እየተገበሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

5/ Ensure that the governance of State-owned enterprises is carried out in a responsible, transparent, and accountable manner and to introduce code of good corporate governance for State-owned enterprises;

፮/ በመንግሥት ባለቤትነት ከተያዙ የልማት ድርጅቶች ፋይናንስ፣ ሂሣብ አያያዝና አሠራር ጋር በተያያዘ ውጤታማ ቁጥጥር እና የሥራ እንቅስቃሴዎችና ክንዋኔ ግምገማ መኖሩን ማረጋገጥ፤

6/ Ensure effective supervision and evaluation of activities and affairs related to the finance, accounting and operations of State-owned enterprises;

፯/ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ውጤታማ በሆነ መንገድ በመፈፀም በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የማምረት አቅም በመጨመር የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ዕድገት ማፋጠን፤

7/ Speeding up the country's economic growth by enhancing the production capacity of state-owned enterprises by carrying out technology transfer effectively

www.abyssinialaw.com

፮/ የፊስካል ዘለቄታማነትን ማሳደግ እና በመንግሥት ባለቤትነት ከተያዙ የልማት ድርጅቶች ጋር የተያያዙ የፊስካል ስጋቶች ውጤታማ በሆነ መንገድ መመራታቸውን ማረጋገጥ፤

፱/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት፣ ለማኅበራዊ ልማት እና ለሥራ ዕድል ፈጠራ ሀገር ዐቀፍ ዓላማዎች አስተዋጽዎ እንዲያደርጉ ማስቻል፤ እና

፲/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች በቅጥር ፖሊሲዎቻቸውና አሠራራቸው በብቃት ላይ የተመሠረተ ሀገራዊ ስብጥርን ያማከለ አካታችና የፆታ እኩልነትን የሚያራምዱ፤ ሙያና አቅም ያላቸውን ሠራተኞች የሚቀጥሩ አሠሪዎች እንዲሆኑ ማድረግ፡፡

8/ Promote fiscal sustainability and ensure that the fiscal risks associated with State-owned enterprises are effectively managed;

9/ Enable State-owned enterprises to contribute to the broader national objectives of economic growth, social development, and job creation; and

10/ Enable State-owned enterprises to be good employers of talented and capable staff based on merits that promote gender parity and country wide composition inclusiveness through their employment policies and practices.

ክፍል ሦስት
በመንግሥት ባለቤትነት የሚያዙ የልማት ድርጅቶች ስለ መቋቋም፣ ሕጋዊ ሰውነት እና ችሎታ

PART THREE
ESTABLISHMENT OF STATE-OWNED ENTERPRISES, LEGAL PERSONALITY AND CAPACITY

፭. በመንግሥት ባለቤትነት የሚያዝ የልማት ድርጅት ምሥረታ

፩/ አዲስ በመንግሥት ባለቤትነት የሚያዝ የልማት ድርጅት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም በመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ሊቋቋም ይችላል፡፡

፪/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚያቋቁመውን በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትን በበላይነት የሚቆጣጠር ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይመድባል::

፫/ በመንግሥት ባለቤትነት የሚያዝ የልማት ድርጅት ከመቋቋሙ በፊት የሚከተሉት መረጋገጥ ይኖርባቸዋል፤

5. Establishment of a State-owned Enterprise

1/ A State-owned enterprise may be established by the Council of Ministers pursuant to the provisions of this Proclamation or by a State holding company.

2/ The Council of Minsters shall designate a supervising authority that oversees State-owned enterprises it establishes.

3/ Before the establishment of a State-owned enterprise, the following shall be ascertained:

www.abyssinialaw.com

ሀ) መንግሥት ድርጅቱን ለማቋቋምና ለማካሄድ አሳማኝ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ምክንያቶች መኖራቸውን፤

a) there is a demonstrable economic and social justification for the Government to be involved in its creation and operation;

ለ) ለማቋቋሚያ ካፒታል በዓይነት የተዋጣ ክፍያ ካለ ዝርዝር የንብረቱን መግለጫ፣ የእያንዳንዱን ንብረት ዋጋ ግምትና የአገማመቱን ዘዴዎች በባለሙያ በትክክል መገመቱን፤ እና

b) if there is any payment in kind as part of the establishment capital, the property is correctly valued by experts who will issue a report containing a detailed description of the property, the value given to each item and the method of valuation; and

ሐ) ለመነሻ ካፒታል ተብሎ የተከፈለ ማናቸውም ጥሬ ገንዘብ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት እንደተቋቋመ በስሙ በተከፈተ የባንክ ሂሣብ መቀመጡን፡፡

c) any cash, paid as part of the initial capital, is deposited in a bank in the name and to the account of the State-owned enterprise upon its establishment.

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫(ለ) ቢኖርም፣ በዓይነት የተፈፀመው ክፍያ አዲት የተደረገ ሂሣብ ካለው በሂሣብ መዝገብ የተመለከተው የዓይነት ክፍያ ሊወሰድ ይችላል፡፡

4/ Notwithstanding Sub-article (3) paragpah (b) of this Article, if the payment made in kind has audited accounts, the book value of such payment in kind may be taken into account.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫)(ለ) የተጠቀሱት ባለሙያዎች በዓይነት የተዋጣውን ንብረቶች ዝርዝር መግለጫ፣ ለእያንዳንዱ ንብረት የተሰጠውን ዋጋ እና የአገማመቱን ዘዴዎች ያካተተ ሪፖርት ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው፣ አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን እና በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት እያንዳንዳቸው የሪፖርቱ ኮፒ እንዲደርሳቸው መደረግ ይኖርበታል፡፡

5/ The experts mentioned under Sub-article (3) paragraph (b) of this Article shall prepare a report containing a detailed description of the property, the value given to each item and the method of valuation. The State holding company or the relevant supervising authority and the State- owned enterprise shall each receive one copy of such report.

www.abyssinialaw.com

፮/ ቀደም ሲል ወይም በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅትን ለማቋቋም መንግሥት ያወጣው አዲት የተደረጉ ማናቸውም ወጪዎች የመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት መነሻ ካፒታል አካል ይሆናሉ፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫(ሐ) ተቀማጭ የሆነው ገንዘብ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት እስከሚያገኝ ወይም ማቋቋሚያው ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እስከሚወጣ ድረስ በዝግ አካውንት የሚቀመጥ ይሆናል።

፮. ማቋቋሚያ ሰነድ ወይም ሕግ

፩/ ባለቤትነቱ ሙሉ በሙሉ ወይም አብላጫ ድርሻው በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት የሚቋቋመው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ነው፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ በዚህ አዋጅ እና በማቋቋሚያ ሕጉ መሠረት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትን ማቋቋም ይችላል፡፡

፫/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት መመሥረቻ ፅሑፍ ወይም ማቋቋሚያ ደንብ፤

ሀ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት ስም፤

ለ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት በዚህ አዋጅ የሚገዛ መሆኑን የሚገልጽ ድንጋጌ፤

ሐ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት የተቋቋመበት የንግዱ ዓላማ እና የሚሳተፍበት አትራፊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች፤

6/ Any audited expenses incurred by the Government prior to and for the establishment of the State-owned enterprise shall form part of the initial capital of the State-owned enterprise.

7/ The initial capital deposited under Sub-article (3) paragraph (c) of this Article shall be deposited in a blocked account until the State-owned enterprise obtains its commercial registration certificate or its establishing regulation is published in the *Negarit Gazette*.

6. Establishment Document or Law

1/ A wholly or majority owned State-owned enterprise shall be established by the regulationof the Council of Ministers.

2/ With out prejudice to Sub-Article (1) of this Article, a State holding company may establish a State-owned enterprise in accordance with this Proclamation and the establishing law of the holding company.

3/ The Memorandum of Association or establishing Regulation of a State-owned enterprise shall contain:

a) the name of the State-owned enterprise;

b) a provision which states that the State-owned enterprise shall be governed by this Proclamation;

c) the business objective for which the State-owned enterprise is established and the for- profit economic activities it will be engaged in;

www.abyssinialaw.com

መ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት እንዲያቀርብ የሚጠበቅበት የሕዝብ አገልግሎት ግዴታ፤

ሠ) የተፈቀደው ካፒታል፤

ረ) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት የተከፈለው ካፒታል መጠን፤

ሰ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት ከጠቅላላ ሀብቱ በላይ ሊጠየቅ እንደማይችል የሚገልጽ ድንጋጌ፤

ሸ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት ዋና መሥሪያ ቤት የሚገኝበት አድራሻ፤

ቀ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት ቅርንጫፍ መክፍት እንደሚችል የሚገልጽ ድንጋጌ፤

በ) የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲፈቅድ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው ድርጅት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው ተቀጥላ ድርጅት የማቋቋም መብት እንዳለው፤

ተ) የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ስም፤እና

ቸ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት የቆይታ ጊዜ፤ መያዝ ይኖርበታል።

d) any public service obligation expected to be delivered by the enterprise;

e) the authorized capital;

f) the amount of paid-up capital both in cash and, if any, in kind;

g) a provision which states that the State-owned enterprise shall not be liable beyond itstotal assets;

h) the address of the State-owned enterprise where its head office shall be situated;

i) a provision which authorizes the State-owned enterprise may open branches;

j) the right of the State-owned enterprise to establish a subsidiary, with its own legal standing upon approval of the State holding company or the Council of Ministers;

k) the name of the State holding company or the relevant supervising authority; and

l) the duration for which the State-owned enterprise is established.

፯. <u>ሕጋዊ ሰውነት እና ተጠያቂነት</u>

፩/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት መብቶችና ግዴታዎች የሚያጎናፅፉት ሕጋዊ ሰውነት ይኖረዋል።

፪/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ካለው ጠቅላላ ሀብት በላይ በዕዳ ተጠያቂ ሊሆን አይችልም።

7. <u>Legal Personality and Liability</u>

1/ A State-owned enterprise shall have a legal personality with rights and obligations.

2/ A State-owned enterprise may not be held liable beyond its total assets.

www.abyssinialaw.com

፰. በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት አድራሻና ድኅረ ገጽ

፩/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት አድራሻ ዋናው መሥሪያ ቤት የሚገኝበት ቦታ ነው።

፪/ ሁሉም በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሚከተሉትን መረጃዎችን የያዘ ድኅረ ገጽ ሊኖራቸው ይገባል።

ሀ) ወቅታዊ የኦዲት ሪፖርትና የኦዲቱ ግኝት፤

ለ) ዓመታዊ ሪፖርት፤

ሐ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት የቦርድና የሥራ አስፈፃሚዎች መረጃዎች፤

መ) ቦርዱ ከንግድና ስትራቴጂክ አንፃር ሚስጥራዊ ናቸው ካላቸው ውጭ ያሉ የቦርድ ቃለ ጉባዔዎችና ውሳኔዎች፤ እና

ሠ) ለሕዝብ ጠቃሚ የሆነ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትን የሚያመለክት ሌላ ማናቸውም መረጃ።

8. Address and Website of the State-owned Enterprise

1/ The address of a State-owned enterprise shall be the place where its head office is situated.

2/ All State-owned enterprises shall maintain a website, and provide access to the following information:

a) the latest audited financial reports including audit result;

b) annual report;

c) information about members of the board and executive officers of the State-owned enterprise;

d) minutes and resolutions of the board, except those containing information the board considers to be commercially or strategically sensitive;

e) any other relevant information on the State-owned enterprise that may be of publicinterest.

፱. ችሎታ

፩/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ እና በመመሥረቻ ጽሑፍ ወይም በማቋቋሚያ ደንቡ ከተመለከቱት የሥራ ዝርዝሮች ጋር ተያያዥ የሆኑ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችለው ችሎታ ይኖረዋል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት፤

ሀ) በራሱ ስም የመክሰስና የመከሰስ እና በግልግል ዳኝነት ፊት ድርጅቱን የመወከል፤

9. Capacity

1/ A State-owned enterprise shall have such capacity, as is necessary, to accomplish its establishment objective and to perform undertakings related to activities stipulated in its Memorandum of Association or establishing Regulation.

2/ Without limiting the generality of Sub-Article (1) of this Article, a State-owned enterprise shall have the capacity to:

a) sue and be sued in its own name and represent itself in arbitration proceedings;

www.abyssinialaw.com

ለ) የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረትን በግዢ ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ የማግኘት፣ ባለይዞታ የመሆን፣ባለቤት የመሆን፣ በማያገሩ የመስጠት፤

ሐ) ውል የመዋዋል፣ግንዘብ የመበደር፤

መ) የንግድና ሌሎች ተመሳሳይ ሰነዶችን የማውጣትና የመቀበል፤

ሠ) የባንክ ሂሣብ የመክፈትና የማንቀሳቀስ፤ እና

ረ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ (ለ) (ሐ) እና (መ) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ኢንቨስት የማድረግ፤ ችሎታ ይኖረዋል።

፫/ ከመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ከተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በቅድሚያ የጽሑፍ ፈቃድ ካልተገኘ በስተቀር በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት የሚከተሉትን ማድረግ አይችልም፤

ሀ) ከአጠቃላይ ሀብቱ ከግ (ሃምሳ) በመቶ በላይ የሆነ ዕዳ ውስጥ መግባት፤

ለ) ተቀጥላ ድርጅትን የማቋቋም፤

ሐ) በጋራ ኢንቨስትመንት መሳተፍ፤

መ) ከኢትዮጵያ ውጭ ማናቸውም መጠን ያለው ኢንቨስትመንት ማድረግ፤ እና

ሠ) ከመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ከተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት የሚጠየቅ በሕግ የተመለከተ ማናቸውንም ነገር።

b) acquire, possess, own, dispose of, pledge and mortgage movable and immovable property;

c) enter into contracts and borrow money;

d) issue and accept commercial and other instruments;

e) open and operate bank accounts; and

f) without prejudice to the provisions of Sub-Article 3 paragraphs (b), (c) and (d) of this Article, invest money.

3/ A State-owned enterprise shall not do any of the following without the prior written approval of a State holding company or relevant supervising authority:

a) Incur a liability that is 50 percent over the amount of its total asset;

b) Incorporate a subsidiary;

c) Engage in joint investment;

d) Make an investment of any amount outside Ethiopia; and

e) Anything that is prescribed by any law as requiring the prior approval of the State holding company or the relevant supervising authority.

www.abyssinialaw.com

ክፍል አራት

በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች ተወዳዳሪነት

፲. ተወዳዳሪነት ያለበት የንግድ ከባባዊ ሁኔታ

፩/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት መንግሥት በባለቤትነት የያዘው በመሆኑ ከሌሎች የንግድ ድርጅቶች በተለየ ተጠቃሚም ሆነ ተጎጂ መሆን የለበትም፡፡

፪/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት መልካም ኮርፖሬት አስተዳደራዊ መዋቅሮች ደንብና ፖሊሲዎች፣ የፋይናንስ ተጠያቂነት እና የሥራ አፈፃፀም አስተዳደር ሥርዓቶች እና እንቅስቃሴው የገበያ ማዛበትን አለማስከተሉን ለማረጋገጥ በዘርፉ ተፈፃሚ የሚሆን የአገላለጽ መስፈርቶችን በመተግበር ተወዳዳሪ በሆነ የንግድ ከባባዊ ሁኔታ ውስጥ መንቀሳቀስ አለበት።

፫/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ተለይቶ የሚታወቅ፣ግልፅ የሆነ እና ተመጣጣኙ ወጪ በመንግሥት የሚሸፈን የሕዝብ አገልግሎት ግዴታ እንዲያቀርብ ግዴታ ሊጣልበት ይችላል፡፡

፲፩. የሕዝብ አገልግሎት ግዴታዎች

፩/ በሚኒስቴሩ አማካኝነት በሚቀርብ የመንግሥት ጥያቄ የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትን ከመመሥረቻ ጽሑፉ ወይም ከማቋቋሚያ ደንቡ ጋር የሚጣጣም የሕዝብ አገልግሎት እንዲሰጥ ወይም እንዲያቆም በጽሑፍ ግዴታ ሊጥልበት ይችላል፡፡

PART FOUR

COMPETITIVE NEUTRALITY OF STATE-OWNED ENTERPRISES

10. Competitive Business Environment

1/ A State-owned enterprise shall neither be advantaged nor disadvantaged compared to other commercial entities as a result of its Government ownership.

2/ A State-owned enterprise shall operate in a competitive business environment by adopting a code of good corporate governance structures and policies, establishing financing, liability and performance management procedures, and introducing sector specific transparency and disclosure requirements to ascertain its activities do not cause market distortion.

3/ Subject to the provisions of this Article, a State-owned enterprise may be obliged to execute a public service obligation in accordance with Sub-Article (2) of Article 11 of this Proclamation with clear identification, disclosure, and adequate compensation by the State.

11. Public Service Obligations

1/ Upon the request of the Government through the Ministry, a State holding company or relevant supervising authority may oblige, in writing, a State-owned enterprise to provide or cease providing a public service obligation that is consistent with the State-owned enterprise's memorandum

www.abyssinialaw.com

of association or establishing Regulation.

፪/ በሚኒስቴሩ በጽሑፍ የሚቀርበው የሕዝብ አገልግሎት ግዴታ ጥያቄ የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት፡

ሀ) የሚቀርበውን የዕቃዎች ወይም የአገልግሎቶች ዓይነት፡

ለ) የሕዝብ አገልግሎቱን ግዴታውን ለመወጣት በመንግሥት ባለቤትነት በተያዘው የልማት ድርጅት ላይ የሚያስከትለው ዓመታዊ አጠቃላይ ወጪ በግምት፡

ሐ) የሕዝብ አገልግሎት ግዴታውን በመወጣት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት የሚገኘው ዓመታዊ ትርፍ ወይም የሚደርስበት ኪሣራ በግምት፡

መ) የገንዘቡን ምንጭ እና የሕዝብ አገልግሎት ግዴታን ለመወጣት ከሚኒስቴሩ ወይም ከሌሎች ምንጮች የተገኘ ፈቃድ፡

ሠ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት የሕዝብ አገልግሎት ግዴታውን በሚወጣበት ጊዜ እንዴት ቁጥጥር እንደሚደረግበትና አፈፃፀሙ እንደሚለካ፤ እና

ረ) የሕዝብ አገልግሎት ግዴታ አፈፃፀም ለሕዝብ ስለሚገለፅበት ዘዴዎች፡፡

2/ A written request of public service obligation by the Ministry shall include:

a) the types of goods or services to be provided;

b) an estimate of the total cost of the goods and / or services and the annual cost to the State-owned enterprise for providing the public service obligation;

c) an estimate of the annual profit to be received or losses to be incurred by the State-owned enterprise for providing the public service obligation;

d) sources of funding and authorization from the Ministry or other sources for the provision of the public service obligation;

e) how the performance of the State-owned enterprise will be monitored and measured in providing the public service obligation; and

f) the means for public disclosure of the public service obligation provided.

፫/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሕዝብ አገልግሎት ግዴታቸውን ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲወጡ ለማስቻል የሚመለከታቸው የፌዴራል እና የክልል የመንግሥት ተቋማት አገልግሎቱ የሚሰጥበትን ምቹ ከባቢያዊ ሁኔታ የመፍጠር እና ተገቢውን ድጋፍ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

3/ Concerned Federal and Regional government organs shall create a conducive environment and render appropriate support, so as to enable State-owned enterprises to perform their public service obligation effectively.

www.abyssinialaw.com

ክፍል አምስት

በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች አስተዳደራዊ መዋቅርና ሥራ አመራር

፲፪. ድርጅታዊ መዋቅር

እያንዳንዱ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት፣

፩/ የዳይሬክተሮች ቦርድ፣

፪/ አንድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች፣ እና

፫/ ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ሠራተኞች፣

ይኖሩታል።

፲፫. የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም የተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባራት

በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ የተሰጠ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን፣

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ እንደተጠበቀ ሆኖ የቦርድ አባላትን ይሾማል፣ ያሰናብታል፣

፪/ በቦርድ አባላት መካከል በብቃት ላይ የተመሠረተ ሀገራዊ ስብጥርን ያማከለ አካታችነት እና የፆታ መመጣጠን እንዲኖር ያደርጋል፣

፫/ የቦርድ አባላትን፣ የቦርዱን ሊቀመንበር እና ምክትል ሊቀመንበር ይሾማል፣

፬/ የቦርድ አባላትን ለመሾምና ለማሰናበት ተፈፃሚ የሚሆኑ ከመልካም የኮርፖሬት አስተዳደር ልምዶች ጋር የሚጣጣሙ መመሪያዎች ያወጣል፣ በተግባር ላይ ያውላል፣

PART FIVE

GOVERNANCE STRUCTURE AND MANAGEMENT OF STATE-OWNED ENTERPRISES

12. Governance Structure

Each State-owned enterprise shall have:

1/ a Board of Directors;

2/ a chief executive officer, and as may be necessary, one or more deputy chief executive officers; and

3/ the necessary staff to perform its functions.

13. Powers and Duties of a State holding company or a Supervising Authority

Without prejudice to the special authority given by another law, A State holding company or relevant supervising authority shall:

1/ Appoint and remove board members subject to Article 15 of this Proclamation;

2/ achieve country wide composition inclusiveness and gender balance based on merits consideration within board members it appoints;

3/ Appoint members,deputy chairman and chairman of a board;

4/ consistent with good corporate governance practices, for appointment and removal criteria of board members;

www.abyssinialaw.com

፭/ በቅድሚያ ስምምነት በተደረሰባቸው የሥራ አፈፃፀም ምዘና መስፈርቶች መሠረት የቦርዱንና የግለሰብ ቦርድ አባልን የሥራ አፈፃፀም በየዓመቱ ይመዝናል፣ እንደአግባቡ ማበረታቻ ይሰጣል ወይም እርምጃ ይወስዳል፣ የቦርድ አባላትን የስብሰባ አበል እና ዓመታዊ ክፍያን ይወስናል፤

5/ Evaluate performance of a board and of individual board members annually based on a pre-agreed set of performance criteria; apply incentives and sanctions as appropriate, and determine the meeting allowance and annual compensation of the board members;

፮/ አግባብ ባለው የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ሕጎች መሠረት መልካም የኮርፖሬት አስተዳደር እና የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ፖሊሲዎች አዘጋጅቶ ያወጣል፤ በመንግሥት ባለቤትነት በተያዙ የልማት ድርጅቶች እየተተገበሩ መሆኑን ይከታተላል፤

6/ Develop and prescribe good corporate governance and financial reporting policies in line with the applicable financial reporting laws, and monitor compliance by State-ownedenterprises;

፯/ ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ወይም በሥራ ላይ እያሉ ስለመልካም የኮርፖሬት አስተዳደር ልምዶች ለሁሉም ቦርድ አባላት ሥልጠና ይሰጣል፤

7/ Arrange training in good corporate governance practices for all board members prior to the commencement of their Board function and during their tenure;

፰/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶችን የሥራ አፈፃፀም ለማሻሻል፣ በሥራቸውም ተጠያቂነትን፣ ግልፅነትንና ተወዳዳሪነትን እንዲኖር ለማድረግ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቶችን አዘጋጅቶ ያወጣል፤

8/ Develop and prescribe financial management systems to improve the performance, accountability, transparency and competitiveness of State-owned enterprises;

፱/ በመንግሥት ባለቤትነት በተያዙ የልማት ድርጅቶች የሚቀርቡ የካፒታል ማሳደግና መቀነስ ጥያቄዎችን ይገመግማል፣ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፳፬ (፩)፣ (፪) እና (፫) መሠረት ውሳኔ ይሰጣል፤

9/ Evaluate and decide on the request of State-owned enterprises on the increase or decrease of their capital in accordance with Sub-Articles (1), (2) and (3) of Article 24 of this Proclamation;

፲/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የመንግሥትን የባለቤትነት ፖሊሲ በመንግሥት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች መሠረት ከሚኒስቴሩ ጋር በመቀናጀት ተግባራዊ ያደርጋል፤

10/ Implement, in accordance with economic policies and program of the Government, the State-owned enterprise ownership policy of the Government in coordination with the Ministry;

www.abyssinialaw.com

፲፩/ የፊስካል ስጋቶችን ለመቀነስ በሚኒስቴሩ የወጡ እርምጃዎችን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፤

11/ Ensure the implementation of measures prescribed by the Ministry to mitigate fiscal risks in accordance with Sub-Article (1) and (2) of Article 22 of this Proclamation;

፲፪/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች ዓመታዊና የረጅም ጊዜ የንግድ ዕቅዶች ማዘጋጀታቸውን እና ፋይናንስ ነክና ፋይናስ ነክ ያልሆኑ የሥራ አፈፃፀም እርምጃዎችንና የንግድ ዕቅዶቹን ለመተግበር እና ስትራቴጂውንና የንግድ ዕቅዱን መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ ቁልፍ የሥራ አፈፃፀም መለኪያዎችንና ግቦችን ጨምሮ የንግድ ዕቅዶችን ተግባራዊ ለማድረግ በየዓመቱ ከቦርድ ጋር የሥራ አፈፃፀም ስምምነት ይፈራረማል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሲሆን የእርምት እርምጃዎች ይወስዳል፤

12/ Ensure that State-owned enterprises develop annual and long-term business plans, and sign each year a performance agreement with a board for the execution of the business plans which includes financial and non-financial performance measures and key performance indicators and targets formulated based on the strategy and business plan, monitor implementation of the same, and take corrective actions as deemed necessary;

፲፫/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች ትክክለኛ ክህሎት፣ ሙያ፣ ልምድና ብቃት ባላቸው ግለሰቦች መመራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል መመሪያ ያወጣል፤

13/ Issue Directive to ensure that State-owned enterprises are managed by individuals with the right skills, expertise, experience and qualifications;

፲፬/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች በዚህ አዋጅ መሠረት ሕጋዊ መጠባበቂያ ገንዘብ እንዲያቋቁሙ ያደርጋል፤

14/ Cause the establishment of a legal reserve fund by State-owned enterprises pursuant to this Proclamation;

፲፭/ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ለተቋቋሙ በመንግሥት ባለቤትነት ለተያዙ የልማት ድርጅቶች በመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም በመንግሥት ገንዘብ መመደቡን እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፬) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ በመንግሥት ባለቤትነት ለተያዙ የልማት

15/ Ensure, where applicable, the allocation of funds by the State holding company or the Government for State owned enterprises established under their respective mandate and purview so that the authorized capital of the

www.abyssinialaw.com

ድርጅቶች የተፈቀደው ካፒታል ሙሉ ለሙሉ መከፈሉን ያረጋግጣል፤

State-owned enterprises shall be fully paid up within the period specified under Article 23 Sub-Article (4) of this Proclamation;

፲፮/ የመንግስት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለስልጣን በመንግሥት በሚፀድቀው የትርፍ ድርሻ ክፍፍል ፖሊሲ መሠረት የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች ለሚኒስቴሩ የሚከፍሉትን የመንግሥት የትርፍ ድርሻ መጠንን ይወስናል፤

16/ Based on government approved Dividend Policy, determine the amount of state dividend to be paid to the Ministry by a State holding company or from State-owned enterprises under the oversight of supervising authorities;

፲፯/ የፋይናንስና የሥራ አፈፃፀም መለኪያዎችን በመጠቀም በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶችን ሥራ አፈፃፀምን ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ ድርጅቶች የሥራ አፈፃፀም ዓመታዊ የተጠቃለለ ሪፖርት በድኅረ ገጹ ያወጣል፡፡

17/ Establish a system to monitor and evaluate the performance of State-owned enterprises using financial and operational performance indicators and publish an annual aggregate report on the performance of State-owned enterprises on its website;

፲፰/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የውጭ ኦዲተሮችን ይሾማል፣ ያሰናብታል፤

18/ Appoint and remove the external auditor of State-owned enterprises;

፲፱/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ ድርጅቶችን የውጭ ኦዲት ሪፖርት ያፀድቃል፣በኢዲት ምርመራ ግኝቶች ላይ እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል፤

19/ Approve external audit report of State-owned enterprises and ensure that corrective measures are taken on audit findings;

፳/ እንደአግባብነቱ በቁጥጥሩ ሥር ያሉትን በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶችን መፍረስ፣ ውህደት ወይም መከፈል ላይ ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ የቁጥጥር ሥልጣንን ወደ ሌላ ባለሥልጣን የማስተላለፍ ውሳኔ ይሰጣል ወይም የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤

20/ Decide or propose, as the case may be, on the dissolution, amalgamation or division of a State- owned enterprise under its control, or the transfer of the State-owned enterprise or its management in any other manner;

www.abyssinialaw.com

፳፩/ በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር ፹፻፸፯/፪ሺ፮ መሠረት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች ሂሣብ ስለሚሰረዙበት መመሪያዎች ለሚኒስቴሩ ሀሣብ ያቀርባል፤ ሲፀድቁም አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤ እና

21/ Propose to the Ministry Directives on writing off the accounts of State-owned enterprises in accordance with the Financial Reporting Proclamation No. 847/2014 and follow up on their implementation upon approval; and

፳፪/ ለቦርዱ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው፣ የመንግሥትን የባለቤትነት መብትን ለማስከበር የሚያስፈልጉ ሌሎች ሥራዎችን ያከናውናል።

22/ Without prejudice to the powers and duties given to the Board, perform other functions necessary for the protection of the ownership rights of the Government.

፲፬. በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ስለማዛወር

14. Privatization of State-Owned Enterprise

፩/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሚሸጡት ወይም ወደ ግል የሚዛወሩት የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር በወጣው አዋጅ ቁጥር ፭ሺ፪፻፺፮/፪ሺ፲፪ መሠረት ነው።

1/ The decision to sell or privatize a State-owned enterprise shall be carried out in accordance with the Privatization Proclamation No.1206/2020.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም፣ የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ የሚያስተዳድራቸውን በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች በመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ቦርድ ፈቃድ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ወደ ግል እንዲዞሩ ሊወስን ይችላል። ሆኖም በመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ሥር ያለ የተለየ የሕዝብ ጥቅም ያለበት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ወደ ግል ሊዞር የሚችለው በመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ቦርድ የሚቀርብ የውሳኔ ሀሣብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲፀድቅ ነው።

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this article; a State holding company can decide to fully or partially privatize the state-owned enterprises it manages with the approval of the board of the State holding company. However, Public Enterprise in which there is a special public interest may be fully or partially privatized only upon approval by the Council of Ministers by taking into consideration the recommendations of the State holding company board.

www.abyssinialaw.com

፫/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ሽያጭ ገቢ አጠቃቀም በሚኒስቴሩ እና በመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ስምምነት ይወሰናል፡፡

፬/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) አፈፃፀም፣ የተለየ የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ዝርዝር በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

3/ Notwithstanding the provision of Sub-article (2) of this Article, the Ministry and the State holding company shall jointly decide on the utilization of the proceeds of the sale of fully or partially privatize a State-owned enterprise.

4/ For the purpose of Sub-Article (2) of this Article, the list of Public Enterprises in which there is a special public interest shall be determined by the Council of Ministers Regulation.

፲፭. ስለቦርድ መቋቋም

15.Formation of the Board

፩/ ማንኛውም በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ የተሰጡትን ኃላፊነቶችን ለመወጣት እና የድርጅቱን ጥቅም ለማስጠበቅ ቦርድ ይኖረዋል፡፡

1/ Any State-owned enterprise shall form a board to carry out its duties and responsibilities as stipulated under Article 17 of this Proclamation.

፪/ ማናቸውም ቦርድ በማናቸውም ጊዜ ሥራውን በመንግሥት ባለቤትነት በተያዘ የልማት ድርጅት ስምና ለድርጅቱ የላቀ ጥቅሞች በተገቢው ጥንቃቄ ማከናወን አለበት፡፡

2/ Board members shall execute their duties and responsibilities with due care and in the name of the State-owned enterprise.

፫/ ቦርዱ ከሚያጋጥሙና ሊያጋጥሙ ከሚችሉ የጥቅም ግጭት ራሱን መጠበቅ ይኖርበታል፡፡

3/ The board shall take all reasonable precautions and measures to prevent actual and potential conflict of interest.

፬/ ቦርዱ፣ የቦርዱ ሊቀመንበሩን እና ምክትል ሊቀመንበሩን ጨምሮ ከአምስት ያላነሱ ከአስራ አንድ ያልበለጡ አባላት ይኖሩታል፡፡

4/ The board members including the chairperson and the deputy chairperson shall be appointed and the number shall be between Five and Eleven.

፭/ አንድ የቦርድ አባል ከሠራተኞች መካከል በሠራተኞች ጠቅላላ ጉባዔ ይመረጣል፡ የሠራተኞች ማኅበር መሪ የቦርድ አባል ሊሆን አይችልም፡፡

5/ One member of the board shall be elected from among the workers by the general assembly of the workers. A leader of a trade union shall not be a member of the board.

www.abyssinialaw.com

፮/ የቦርድ አባላት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት በመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም በተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የወጣውን የሹመት መስፈርት እና መመሪያዎችን የሚያሟሉ መሆን አለባቸው።

6/ Board members shall be appointed on merit and shall meet 'fit and proper criteria', as set out by a State holding company or the relevant supervising authority pursuant to Sub-Article (4) of Article 13 of this Proclamation.

፯/ የቦርድ አባላት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘን የልማት ድርጅት ዓላማውን ለማሳካት የሚያግዝ የትምህርት ደረጃ፣ ክህሎትና ልምድ ያላቸው መሆን አለባቸው።

7/ Board members must have the educational qualification, experience and skill necessary for the achievement of the objectives of the State-owned enterprise they serve.

፰/ ከአጠቃላይ የቦርድ አባላት ከአንድ ሦስተኛ ያላነሱት አግባብነት ያለው ሙያ እና ከአምስት ዓመት ያላነሰ ልምድ ያላቸው ገለልተኛ የቦርድ አባላት መሆን አለባቸው።

8/ Not less than one-third of the total board members shall be independent board members with a minimum Five years of experience, drawn from diverse professional backgrounds.

፱/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፭ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የቦርድ አባላት ከዚህ በተጨማሪ መልካም ስም ያላቸው እና ለሹመት ከመታጨታቸው በፊት ላሉት ሦስት ዓመታት በቦርድ አባልነት ለሚሾሙበት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ሠራተኞች ያልነበሩ፣ በመንግሥት ባለቤትነት ከተያዘው የልማት ድርጅት ጥቅሞች ጋር የሚጋጭ የገንዘብ፣ ቤተሰባዊ፣ የንብረት፣ የሙያ እና ትርጉም ያለው ግንኙነት ጨምሮ ማናቸውም የግል ጥቅም ያልነበራቸው መሆን ይኖርባቸዋል።

9/ Without prejudice to the provisions Sub-Article (5) of this Article, board members shall be of sound reputation and shall not have been an employee of the State-owned enterprise they are appointed to serve in the past three years. They also must not have left the enterprise in bad terms, with no material interest including financial, familial or of proprietary nature, with no professional relationship, and with no conflict of interest to the State-owned enterprise.

፲/ ማንኛውም የቦርድ አባል ከሁለት ለማይበልጡ ተወዳዳሪ ላልሆኑ በመንግሥት ባለቤትነት ለተያዙ ሌሎች የልማት ድርጅቶች በተመሳሳይ ጊዜ በቦርድ አባልነት በመሾም ሊያገለግል ይችላል።

10/ Any board member may also be appointed to act as a member of the board of any other non- competing State-owned enterprise, with a maximum of up to Two board memberships.

www.abyssinialaw.com

፲፩/ የቦርድ አባል የሚሾመው ለሦስት ዓመት የሥራ ዘመን ሆኖ ለሁለተኛ ጊዜ እንደገና ሊሾም ይችላል፡፡ የቦርዱ የሥራ እንቅስቃሴ ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን በአንድ ጊዜ እንዲያበቃ አይደረግም፡፡

11/ A board member shall be appointed for a term of Three years and may be reappointed for a second term. In order to maintain the continuity of the activities of the board, the term of office of its members shall not expire at the same time.

፲፪/ ማንኛውም የቦርድ አባል ከሥራው በፈቃደኝነት ሲለቅ በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት በለቀቀው የቦርድ አባል ምትክ ለቀሪው የሥራ ዘመን የሚያገለግል ሌላ የቦርድ አባል እንዲሾም ቦርዱ ጉዳዩን ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በአምስት ቀናት ውስጥ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

12/ Where any board member resigns from the board, the board shall bring the matter to the attention of the State holding company or the relevant supervising authority within Five days so that a replacement director is appointed pursuant to the provisions of this Article to serve the remaining time of the resigning board member.

፲፫/ የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በቂና አሳማኝ ምክንያቶች ሲኖሩ ለአባልነት የማይመጥንን አንድን የቦርድ አባል በማናቸውም ጊዜ በጽሑፍ ከቦርድ አባልነት ሊያነሳው ይችላል፡፡ ይህ ድንጋጌ በሠራተኛ በተመረጠ የቦርድ አባል ላይ ተፈፃሚ የሚሆን እንደሆነ፣ ተተኪ የቦርድ አባል እንዲመርጥ የቦርድ አባሉን መሰናበት ጠቅላላ ጉባዔው እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

13/ A State holding company or the relevant supervising authority may, at any time, remove a board member in writing where there are sufficient and justifiable grounds that make the member unfit to be a member. Where this provision is applied to a board member elected by workers, the general assembly of the workers shall be notified of the removal who shall then elect a replacement board member.

፲፬/ የሁሉም ቦርድ አባላት ሹመት፣ ስንብትና መልቀቂያ ሁኔታው በተከሰተ በ፲ የሥራ ቀናት ውስጥ ሹመቱ፣ ስንብቱ ወይም መልቀቂያው እንደአግባቡ በመንግሥት ባለቤትነት በተያዘው የልማት ድርጅት ወይም አግባብ ባለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ድኅረ ገጽ መውጣት ይኖርበታል፡፡

14/ All board appointments, removals and resignations shall be published on the website of the State-owned enterprise or the relevant supervising authority, as the case may be, within 10 business days of the appointment, removal or resignation of a board member.

www.abyssinialaw.com

፲፮. የቦርድ ስብሰባ እና የስብሰባ ሥነ ሥርዓት

፩/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት ሥራ ከመጀመሩ በፊት ያለውን ጊዜ ጨምሮ ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም፣ የቦርዱ ሊቀመንበር አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም ወይም ቢያንስ ሁለት የቦርድ አባላት ሲጠይቁ በማናቸውም ጊዜ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

፫/ የቦርዱ አጀንዳ ከስብሰባው ቀን ቢያንስ ከሦስት ቀናት አስቀድሞ ሁሉም አባላት እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የቦርድ ስብሰባ በሊቀመንበሩ የተጠራ እንደሆነ የቦርዱ ስብሰባው አጀንዳ ከስብሰባው ጥሪ ጋር እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል፡፡

፬/ ሊቀመንበሩ፣ ሊቀመንበሩ በሌለበት ምክትል ሊቀመንበሩ ወይም ሁለቱም በሌሉበት ሊቀመንበሩ የሚወክለው የቦርድ አባል ጨምሮ በማገልገል ላይ ያሉ ከግማሽ በላይ የቦርድ አባላት በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔው ይሆናል፡፡

፭/ የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል፡፡ ድምፅ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ የቦርዱ ሊቀመንበር ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

፮/ ቦርዱ ለሥራው ድጋፍ የሚያደርግለት የቦርድ ፀሐፊ ይቀጥራል፡፡

፯/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚ በቦርድ ስብሰባ ይሳተፋል፤ሆኖም ድምፅ የመስጠት መብት አይኖረውም፡፡

16. Board Meetings and Procedures

1/ The board shall meet at least once every month, including prior to the State-owned enterprise becoming operational.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, the board chairman shall call a meeting of the board at any time in cases of urgency or where at least Two board members so request.

3/ The agenda of a board meeting shall be communicated to all members at least Three days before the meeting. If the board meeting is called by the board chairman pursuant to Sub- Article (2) of this Article, the agenda of the board meeting shall be communicated at the same time the meeting is called by the board chairman.

4/ There shall be a quorum when a majority of board members including the chairperson,deputy chairperson, when chairperson is not present or where both are not present, board member appointed by the chairperson then serving are present.

5/ The board shall take decision by majority vote. In case of a tie, the board chairperson shall havea casting vote.

6/ The board shall hire a Board secretary to provide operational support to the Board.

7/ The chief executive officer of a State-owned enterprise may attend board meetings but shall not have the right to vote.

www.abyssinialaw.com

፰/ ቦርዱ ለእያንዳንዱ ስብሰባ በስብሰባው የተገኙ አባላት የፈረሙበት ቃለ ጉባዔ ይይዛል፡፡

፱/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል፡፡

፲፯. <u>የቦርዱ ተግባራትና ኃላፊነቶች</u>

፩/ ቦርዱ፣

ሀ) ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን እንዲፀድቁ ከሚቀርቡት በስተቀር፣ ግልፅ ከሆነ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የፋይናንስ ዕቅድ፣ ቁልፍ የሥራ አፈፃፀም መለኪያዎች እና ስትራቴጂክ አቅጣጫ ያካተተ የኮርፖሬት ፖሊሲንና የንግድ ዕቅድን ያፀድቃል፤

ለ) ከመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም አግባብ ካለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ጋር በመመካከር ብቃትንና በዘርፉ ያለውን ልምድን ጨምሮ ችሎታን እና በግልፅ በተቀመጠ የምልመላ መስፈርቶችን መሠረት ባደረገ በውድድር ላይ በተመሠረተ የምልመላ ሂደት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚን ይሾማል፣ ከሥራ ያሰናብታል፤

ሐ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት መዋቅር፣ የደመወዝ እርከን፣ አበልና ጥቅማ ጥቅሞችን በመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም አግባብ ባለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን እንዲወሰን የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤

8/ The board shall keep minutes for every meeting, which shall be signed by the members present.

9/ Without prejudice to this Article, the board shall draw its own rules of procedure.

17. <u>Powers, Duties and Responsibilities of the Board</u>

1/ The board shall:

a) approve the corporate policy and business plan with clear financing plan and set Key Performance Indicators and the strategic direction of State-owned enterprises other than those matters to be submitted to the State holding company or the relevant supervising authority for approval;

b) in consultation with the State holding company or the relevant supervising authority, appoint the chief executive officer of the State-owned enterprise on a merit-based, competitive selection process with clearly defined selection criteria including qualifications and sector experience, and dismiss the same;

c) consider the structure, salary scale, allowances and benefits of the State-owned enterprise and submit with a recommendation to a State holding company or the relevant supervising authority;

www.abyssinialaw.com

መ) ከመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም አግባብ ካለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ጋር በመካከር ዋና ሥራ አስፈፃሚው፣ የሥራ አመራር አባላትና ሠራተኞች በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት የሥራ አፈፃፀምንና ትርፋማነትን መሠረት በማድረግ ማበረታቻና የደመወዝ ጭማሪ እንዲያገኙ ያደረጋል፤

d) in consultation with a State holding company or relevant supervising authority, incentivize the chief executive officer, management team and staff of the State-owned enterprise based on the performance and profit of the State-owned enterprise;

ሠ) ለዋናው ሥራ አስፈፃሚ ተጠሪ የሆኑ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ኃላፊዎችን ምደባና ስንብት ያፀድቃል፤

e) approve the employment, assignment and dismissal of those officers of the State-owned enterprise directly accountable to the chief executive officer;

ረ) ዋነኛ የድርጊት ዕቅዶችን፣ የስጋት አስተዳደር እና ትግበራ ፖሊሲንና ሥርዓቶችን ይገመግማል፣ አመራር ይሰጣል፤

f) review and provide guidance on major action plans, risk management and compliance policy and procedures;

ሰ) በመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ባለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ባወጣው ማዕቀፍ መሠረት ዓመታዊ በጀትን ያፀድቃል፣ የሥራ አፈፃፀም ዓላማዎችን ይደነግጋል፤

g) approve annual budgets and set performance objectives in line with the framework established by the State holding company or the relevant supervising authority;

ሸ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትን የውስጥ ደንቦች እንዲሁም የሥራ ፕሮግራም ያፀድቃል፣ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፤

h) approve and monitor the internal regulations of the State-owned enterprise as well as its work program;

ቀ) ከመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም አግባብ ካለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ጋር በመካከር ከፀደቀው የንግድ ዕቅድ ጋር የተጣጣመ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ብድርን እና በመያዣነት የሚሰጥ የማይንቀሳቀስና የሚንቀሳቀስ ንብረት ያፀድቃል፤

i) in consultation with a State holding company or the relevant supervising authority, approve borrowing of the State-owned enterprise that are consistent with the adopted business plan and the transfer of immovable and movable property as collatera

www.abyssinialaw.com

በ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ንብረት በአግባቡ መጠበቁን ያረጋግጣል፣ በመንግሥት ባለቤትነት በተያዘ የልማት ድርጅት የሥራ እንቅስቃሴዎች ላይ ተጽዕኖ የማያሳድር የቋሚ ንብረት ሽያጭን ያፀድቃል፤

ተ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት የሂሣብ መዝገብ የድርጅቱን የሂሣብ አያያዝና ተፈፃሚነት ያላቸው የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት በተከተለ መንገድ በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል፤

ቸ) የሂሣብ መዝገብ በመንግሥት ባለቤትነት ለተያዘ የልማት ድርጅት ኦዲተሮች እና ለዋናው ኦዲተር እና በሚወስነው የመዝገብ አቀራረብ መሠረት የድርጅቱን ወቅታዊ የፋይናንስና ሌሎች ሪፖርቶች ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ያቀርባል፤

ኀ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትን የሩብ ዓመት፣ የመንፈቅና ዓመታዊ የሂሣብ መግለጫዎችን ዓለም ዐቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግ ያፀድቃል፤

ነ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትን የሥራ እንቅስቃሴ ወቅታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት እና ሌሎች ማናቸውንም ሪፖርቶች በሚወስነው የሪፖርት አቀራረብ መሠረት ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ያቀርባል፤

j) ensure the proper handling of the assets of State-owned enterprises, approve the sale of fixed assets that may not affect the operations of the State-owned enterprise;

k) ensure State-owned enterprise books of accounts are kept properly in a manner that ascertains the integrity of the State-owned enterprise's accounting and applicable financial reporting system;

l) submit books of account to the auditors of the State-owned enterprise and the Auditor General, and periodic financial and any other reports of the State-owned enterprise to the State holding company or the relevant supervising authority in such manner it shall prescribe;

m) approve quarterly, semi-annual and annual financial statements of the State-owned enterprise in accordance with international financial reporting standards;

n) submit periodic performance report on the operations of the State-owned enterprise and any other reports of the State-owned enterprise to the State holding company or the relevant supervising authority in such manner it shall prescribe

www.abyssinialaw.com

ኘ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ዕዳን የመቋቋም አቅምን ለኢንዱስትሪው በተቀመጡ ደረጃዎች መሠረት ለማስተዳደር በዘርፉ ተፈፃሚ የሚሆን ዘላቂ የዕዳና የሀብት ቀመር እንዲወሰን ያደርጋል፤

አ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ካፒታል መጨመርንና መቀነስን በተመለከተ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሀሣብ ያቀርባል፤

ከ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ቦርድና ሠራተኞች የሚተዳደሩበት የሥነ ምግባር መመሪያ ያፀድቃል፤ ይዘቱንና አፈፃፀሙን ቢያንስ በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ ይገመግማል፤

ኸ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት የመንግሥት አገልግሎት ግዴታዎች አፈፃፀምና ስኬት በመደበኛነት ለሕዝብ መረጃዎች መተላለፋቸውን ያረጋግጣል፤

ወ) በመንግሥት ባለቤትነት በተያዘ የልማት ድርጅት ንብረት ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀምን ጨምሮ የቦርድ አባላትንና የሥራ ኃላፊዎችን የጥቅም ግጭት ጉዳዮችን ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

ዘ) አግባብነት አለው ብሎ በሚወስነው መሠረት ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሪፖርቶችን ወይም ሌሎች ማናቸውንም ሰነዶች ያቀርባል፡፡

o) cause the determination of sector specific sustainable debt/equity ratio of the State-owned enterprise in line with industry standard to manage debt viability of the State-owned enterprise;

p) pursuant to Sub-Article (9) of Article 13 of this Proclamation, propose to the State holding company or the relevant supervising authority the increase or decrease of the capital of the State-owned enterprise;

q) establish and approve a code of conduct governing the board and employees of State- owned enterprises and review the content and operation of the code at least once every Two years;

r) ensure regular public communications on the State-owned enterprise performance and fulfillment of public service obligations;

s) monitor and manage conflicts of interest of board members and officers of the State- owned enterprise including misuse and abuse of assets of the State-owned enterprise;

t) submit reports, results or any documents to a State holding company or the relevant supervising authority in such a manner it shall prescribe;

www.abyssinialaw.com

ገ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት የተቋቋመበት ዓላማዎች ከግብ ማድረሱን ለማረጋገጥ ተገቢውን እርምጃዎች ይወስዳል፤

u) take all reasonable steps to ensure that the State-owned enterprise achieves its establishment objectives;

የ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት የሚገባውን የዕዳ መክፈያው በሚደርስበት ወይም መክፈል በሚኖርበት ጊዜ መክፈል የማይችል የሆነ እንደሆነ ድርጅቱ ዕዳ ውስጥ እንዳይገባ ተገቢውን እርምጃዎች ሁሉ ይወስዳል፤

v) take all reasonable steps to ensure that the State-owned enterprise does not incur a debt if incurring the debt may result in the State-owned enterprise becoming unable to pay all its debts as and when they become due and payable.

ደ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች ለምርምርና ልማት እንዲሁም ለቴክኖሎጂ ሽግግር በጀት የሚመደቡበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ የምርምሩን ግኝቶችንም ያሰራጫል፤

w) Facilitate conditions under which State-owned enterprises allocate budget for research and development and technology transfer, disseminate findings of the research;

፪/ ቦርዱ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትንና ካለ የተቀጥላ ድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴን፣ ስትራቴጂክ አቅጣጫዎችን እና የፋይናንስ ትንበያዎችን የያዘ በበጀት ዓመቱ (፩ኛ ዓመት) እና በቀጣዮቹ የበጀት ዓመታት (፩ኛ እና ፪ኛ ዓመት) ላይ ተፈፃሚ የሚሆን የንግድ ዕቅድ ያፀድቃል፤

2/ The board shall adopt, at the start of each financial year, a business plan that contains information about the operations, strategic direction, and financial projections of the State- owned enterprise, and its subsidiaries if any, that applies to the financial year (“year 1”) and to the following two financial years (“years 1 and 2”).

፫/ የንግድ ዕቅዱና በዕቅዱ የተካተቱት መረጃዎች በመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ከወጡት መስፈርቶች ጋር የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል።

3/ The business plan and information presented in it shall comply with the requirements specified by the State holding company or the relevant supervising authority.

www.abyssinialaw.com

፬/ ቦርዱ፤

ሀ) ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የበጀት ዓመቱ ከመጀመሩ ቢያንስ ከሦስት ወር በፊት በበጀት ዓመቱ (፩ኛ ዓመት) ተፈፃሚ የሚሆነውን የመጨረሻውን የንግድ ዕቅድ ረቂቅ ያቀርባል፤

ለ) ከመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ካለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በረቂቁ ላይ የተሰጡ አስተያየቶችን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ የንግድ ዕቅዱን ማፅደቅ አይችልም፤

ሐ) የንግድ ዕቅዱን ባፀደቀ በ፲ የሥራ ቀናት ውስጥ ኮፒውን ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ያቀርባል፡፡

፭/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት የንግድ ዕቅዱን በማናቸውም ጊዜ ማሻሻል ይችላል፤ ሆኖም ቦርዱ፤

ሀ) የተሻሻለውን የመጨረሻ ረቂቅ ከማፅደቁ ቢያንስ ከሁለት ወር በፊት ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፤

ለ) ከመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ካለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በረቂቁ ላይ የተሰጡ አስተያየቶችን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ማሻሻያውን ማፅደቅ አይችልም፤

4/ The Board shall:

a) avail the State holding company or the relevant supervising authority a final draft of the business plan not less than three months before the start of the financial year to which it will apply (year 1);

b) not approve or adopt the business plan without first taking into account any comment by the State holding company or the relevant supervising authority on the draft;

c) give the State holding company or the relevant supervising authority a copy of the business plan within 10 working days of approving or adopting it.

5/ A State-owned enterprise may amend its business plan at any time, but the Board shall:

a) avail the State holding company or the relevant supervising authority a final draft of the amendment not less than two months before it approves or adopts it;

b) not approve or adopt the amendment without first taking into account any comment by the State holding company or the relevant supervising authority on the draft;

www.abyssinialaw.com

ሐ) ማሻሻያውን ባፀደቀ በ፲ የሥራ ቀናት ውስጥ ኮፒውን ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ያቀርባል፡፡

c) give the State holding company or the relevant supervising authority a copy of the amendment within 10 working days of approving or adopting it.

፲፰. የቦርድ አባላት ተግባራትና ኃላፊነቶች

18. **Duties and Responsibilities of Board Members**

፩/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት የቦርድ አባላት፡

1/ Board members of a State-owned enterprise shall:

ሀ) ንግድ ሕጉን እና ተፈፃሚነት ያለውን የመልካም ኮርፖሬት አስተዳደርን መሠረት በማድረግ ኃላፊነቶቹን በቅን ልቦናና በመንግሥት ባለቤትነት ለተያዘው የልማት ድርጅት የላቀ ጥቅም በተገቢው ጥንቃቄና ትጋት ማከናወን አለበት፤

a) act in good faith and in the best interest of the State-owned enterprise in discharging its responsibilities and act with reasonable care and diligence in line with the provisions of the Commercial Code and the applicable code of good corporate governance;

ለ) በቦርድ አባልነታቸው ምክንያት ያገኙትን መረጃዎች አለአግባብ ጥቅም ላይ ማዋል አይችልም፤

b) not use improperly obtained information as a result of their position as members;

ሐ) በመንግሥት ባለቤትነት በተያዘው የልማት ድርጅት ቦርድ አባልነታቸው ተግባራቸውን ወይም ሥራቸውን በተገቢው መንገድ እንዳያከናውኑ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉባቸውን ማናቸውንም የጥቅም ግጭቶች ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

c) disclose to the board of the State-owned enterprise and the State holding company or the relevant supervising authority any conflicting interest that may hinder the proper performance of their duties and functions as board members of the State-owned enterprise.

www.abyssinialaw.com

፪/ ማናቸውም የቦርድ አባል በዚህ አዋጅ መሠረት ሥራውን ሳያከናውን የቀረ እንደሆነ ተግባሩን ባለመወጣቱ ምክንያት በመንግሥት ባለቤትነት በተያዘው የልማት ድርጅት ላይ ለደረሰው ኪሣራ ወይም ጉዳት በንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

2/ If a board member does not perform his duties in accordance with this Proclamation, he may be held liable for any resulting loss or harm to the State-owned enterprise by reason of breach of duty pursuant to the provisions of the Commercial Code.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ቢኖርም፣ ለኪሣራው ወይም ለጉዳቱን ምክንያት የሆነው ውሳኔ ሲተላለፍ ተቃውሞውን ያስመዘገበ የቦርድ አባል ተጠያቂ አይሆንም፡፡

3/ Notwithstanding Sub-article (2) of this Article, a board member shall not be liable when he has dissented from the decision of the board which caused damage.

፲፱. የቦርድ ኮሚቴዎች

19.Board Committees

፩/ ቦርዱ የተወሰነ ሥራ ለማከናወን አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ሚናዎቹና ኃላፊነቶቹ በግልፅ የተቀመጡለት የኦዲት፣ የስጋት አስተዳደር፣ የሥነ ምግባር እና ሌሎች ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ያቋቁማል፡፡

1/ The board shall establish an audit, risk, ethics and other standing or ad hoc committees as it deems necessary to perform specific duties where the committees' roles and responsibilities are clearly defined.

፪/ የኦዲትና የስጋት አስተዳደር ኮሚቴ ቢያንስ ተገቢው የፋይናንስ ልምድ ያለው አንድ አባልን በሚያካትት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፮) የተደነገጉትን መስፈርቶች በሚያሟላ ገለልተኛ የቦርድ አባል ሊቀመንበርነት መመራት ይኖርበታል፡፡

2/ The audit and risk management committee shall be chaired by an independent board member meeting the requirements provided in Article 15 sub-article (6) of this Proclamation, with at least one member of the committee required to have relevant financial experience.

፫/ በቦርዱ ጥያቄ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት የሥራ አስፈፃሚ አመራር በቦርድ ኮሚቴ ስብሰባዎች ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡

3/ If requested by the board, the executive management of a State-owned enterprise may participate in board committee meetings

www.abyssinialaw.com

፳. የዋና ሥራ አስፈፃሚው ሥልጣን፣ ተግባራትና ተጠያቂነት

፩/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚ ተጠሪነቱ በመንግሥት ባለቤትነት ለተያዘው የልማት ድርጅት ቦርድ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

ሀ) ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎች ከፀደቁለት በኋላ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

ለ) ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚያደርገው ግንኙነቶች ሁሉ እና ድርጅቱ በሚከሰስበትና በሚከሰስበት ጉዳይ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት ይወክላል ወይም ድርጅቱ በሚከሰስበት ወይም በሚከሰስበት ጉዳይ በእርሱ ስም የሚቀርብ ሕጋዊ ተወካይን ይሾማል፤

ሐ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት የሥራ ኃላፊዎች ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ያሰናብታል፤ በቦርድ መፅደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ መዘርዝራቸውን ይወስናል፤

መ) በመንግሥት ባለቤትነት በተያዘው የልማት ድርጅት የውስጥ ደንቦችና አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የድርጅቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ያሰናብታል፤ ደሞዛቸውንና አበላቸውን ይወስናል፤

20. Powers, Duties and Liabilities of the Chief Executive Officer

1/ The chief executive officer of a State-owned enterprise shall be accountable to the board of the State-owned enterprise and shall have the following powers and duties:

a) organize, direct, administer and control the State-owned enterprise following strategies and policies approved by the board;

b) represent the State-owned enterprise in all dealings with third parties and in legal proceedings brought by or against it or delegate a legal representative to act on its behalf in legal proceedings brought by or against it;

c) employ, assign and dismiss executive officers of the State-owned enterprise and define their functions subject to the approval of the board;

d) employ, assign and dismiss other employees of the State-owned enterprise in accordance with the internal Regulations of the State-owned enterprise and relevant laws, and determine their salaries and allowances;

www.abyssinialaw.com

ሠ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት አግባብነት ያለውን የሂሣብ መዝገብ ይይዛል፤ በዓለም ዐቀፍ የፋይናንስ የሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት የሂሣብ መግለጫዎች ያዘጋጃል፤

ረ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፣ ይዘጋል፤ ሆኖም የባንክ ሂሳቡን ሲከፍት ወይም ሲዘጋ ለቦርድ ያሳውቃል፤

ሰ) የገንዘቡ ጣሪያ ቦርዱ በሚያወጣው በመመሪያ የሚወሰን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በበጀቱ በተፈቀደው እና ከንግድ ዕቅዱ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በመንግሥት ባለቤትነት ለተያዘው የልማት ድርጅት የሥራ ማከናወኛ ካፒታል ከስድስት እስከ አሥራ ስምንት ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ የሚከፈል የአጭር ጊዜ ብድር ስምምነት መዋዋል ይችላል፤

ሸ) በቦርድ ሲፀድቅለት ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ገንዘብ መበደር ይችላል፤

ቀ) የአጭር ወይም የረዥም ጊዜ የብድር ውሎች ለመዋዋል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሰ) እና (ሸ) መሠረት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ መስጠት ይችላል፤

e) keep proper books of accounts of the State-owned enterprise and prepare financial statements according to the International Financial Reporting Standards;

f) open, operate, and close bank accounts for the State-owned enterprise and report to the board when opening and closing bank accounts;

g) enter into short-term loan contracts that will be paid between six to eighteen months for the purpose of providing the working capital of the State-owned enterprise as authorized in the budget and consistent with the business plan provided that the maximum amount of money borrowed by the chief executive officer shall be determined by the Directive issued by the board;

h) borrow money on a long-term basis with the approval of the board,

i) pursuant to sub-article (1) paragraphs (g) and (h) of this Article, pledge or mortgage movable or immovable property of the State-owned enterprise for the purpose of entering into short and long-term loan contracts;

www.abyssinialaw.com

በ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት የውስጥ ደንቦች እንዲሁም የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርድ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

j) prepare and submit to the board the internal regulations as well as the work program and budget of the State-owned enterprise, and implement same upon approval;

ተ) በመንግሥት ባለቤትነት በተያዘው የልማት ድርጅት የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ተፅዕኖ በማያደርስ ሁኔታ ቋሚ ንብረቶችን ከንግድ ዕቅዱ በተጣጣመ ሁኔታ ቦርዱን በማስፈቀድ ሊሸጥ ይችላል፤

k) where authorized by the board and consistent with the adopted business plan, sell fixed assets that may not affect the operations of the State-owned enterprise;

ቸ) የቦርዱን ውሳኔዎች ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፤

l) implement and cause the implementation of the decisions of the board;

ኀ) ቦርዱ በሚወስነው መሠረት ሪፖርቶችን ለቦርድ ያቀርባል፤

m) submit reports to the board in such manner as it shall prescribe;

ነ) በመንግሥት ባለቤትነት ለተያዘው የልማት ድርጅት የሥራ እንቅስቃሴ አስፈላጊ በሆነ መጠን ሥልጣኑን ለድርጅቱ ሥራ ኃላፊዎች ወይም ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ይሰጣል፤

n) delegate powers to the officers and other employees of the State-owned enterprise to the extent deemed necessary to the operation of the State-owned enterprise;

ኘ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ምክር የሚሰጥ የሥራ አመራር ኮሚቴ ያቋቁማል፣ ስብሰባዎችንም በሰብሳቢነት ይመራል፤

o) establish, and preside over the meetings of a management committee that shall advise on the operations of the State-owned enterprise; and

አ) በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል፡፡

p) perform other duties assigned by the board.

፪/ ዋና ሥራ አስፈፃሚው በቸልተኝነት ወይም ሆነ ብሎ በመንግሥት ባለቤትነት በተያዘው የልማት ድርጅት ላይ ላደረሰው ጉዳት አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

2/ The chief executive officer shall be liable, in accordance with applicable law, for damages he causes to the State-owned enterprise through negligence or intentionally.

www.abyssinialaw.com

፳፩. ውክልና

በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት በዋና ሥራ አስፈፃሚው እና በዚህ ሕግ መሠረት ሥልጣን በተሰጣቸው ሌሎች ተወካዮች አማካይነት ሥራውን ያከናውናል፤ መብቶቹን ይጎናፀፋል፣ ግዴታ ይገባል።

ክፍል ስድስት

የሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር

፳፪. የሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር

፩/ ሚኒስቴሩ

ሀ) በተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሥር ያሉ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች ውስጥ መንግሥት የሚኖረውን የባለቤትነት መብት በተመለከተ የመንግሥት ተወካይ በመሆን የመንግሥትን አክስዮን በባለቤትነት ይይዛል።

ለ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት በመንግሥት ፋይናንስ ላይ የሚኖረው ተፅዕኖን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ተጽዕኖው እንዲቀንስ ያደርጋል፤ የመንግሥት ሀብትንና ንብረትን በተለይም የመንግሥት አገልግሎት ግዴታዎችን በመወጣት ሂደት ከሚፈጠር የፊሲካል ስጋቶች ይጠብቃል፤

ሐ) ሊያጋጥሙ የሚችሉ የፊስካል ስጋቶችን ለመከታተልና ለመገምገም አስፈላጊ የሆኑ የቦርድ ኮሚቴዎች ሪፖርቶችን ጨምሮ መረጃዎችንና ሪፖርቶችን ሁሉ በመንግሥት ባለቤትነት ከተያዙ የልማት ድርጅቶች ይሰበስባል፤

21. Agency

A State-owned enterprise shall carry out its activities, acquire rights and incur liabilities through its chief executive officer and other agents authorized in accordance with this Proclamation.

PART SIX

POWERS AND DUTIES OF THE MINISTRY

22. Powers and Duties of the Ministry

1/ The Ministry shall:

a) acting as a representative of the Government, owns the shares of the government as the custodian of Government's ownership rights in State-owned enterprises that are under the regulatory authority;

b) monitor, analyze, and mitigate the impacts of State-owned enterprises on public finances and ensure effective safeguarding of public resources and assets including the fiscal risks caused by the fulfillment of public service obligations;

c) collect from State-owned enterprises all data and reports necessary to monitor and analyze the potential fiscal risks including board committee reports;

www.abyssinialaw.com

መ) ከሰበሰበው መረጃና ሪፖርቶች በመነሳት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትን የዕዳ ሸክም እና ዕዳው በመንግሥት ፋይናንስ ላይ የሚኖረውን ተዕዕኖ በተመለከተ የግምገማ ሪፖርት ያዘጋጃል፤ ሪፖርቱን በመገምገም የፊስካል ስጋቶች መቀነሻ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

d) on the basis of data and reports received, prepare an assessment of the State-owned enterprise debt burdens and impact on public finances and take mitigating measures for the fiscal risks;

ሠ) የድርጅቶቹን የፊስካል ስጋቶችና በመንግሥት ሂሣቦች ላይ ስለሚኖራቸውን እምቅ ተዕዕኖ ዓመታዊ ሪፖርት፣ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት የተሰማራበት ዘርፍን የፋይናንስ ሁኔታ የሩብ ዓመት ሪፖርቶች እና ሁኔታው በሚያስገድድበት ጊዜ ለሚመለከተው በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት በአድራሻው የሚላክ የስጋቶች መቀነሻ እርምጃዎች ሪፖርት ያዘጋጃል፤ እና

e) produce an annual report on fiscal risks of enterprises and their potential implications for government accounts; quarterly reports on the financial situation of the State-owned enterprise sector; and reports on risk mitigation addressed to individual State-owned enterprises, when the situation so requires; and

ረ) የአደጋ ስጋት ግምገማና የመቀነሻ እርምጃዎች ሪፖርቶች ያወጣል፣ በመንግሥት ባለቤትነት ለተያዙ የልማት ድርጅቶች፣ ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን፣ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት፣ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር አግባብነት ላለው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ሪፖርቶቹን በሚኒስቴሩ ድኅረ ገጽ ላይ ያወጣል።

f) publish fiscal risk evaluation and risk mitigation reports and submit to State-owned enterprises, the State holding company or the relevant supervising authority, the Office of the Prime Minister, the Federal Auditor General, and to to the relevant standing committee(s) of the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and publish them on the official website of the Ministry.

www.abyssinialaw.com

፪/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት በከፍተኛ ደረጃ ለፋይናንስ እጥረት ተጋላጭ ሆኖ ወይም እጥረት አጋጥሞት ከተገኘ ሚኒስቴሩ፤

ሀ) በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የድርጅቱን የፋይናንስ አቋም እንዲያሻሽል ግምገማውንና በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት እና የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ከሚወስዷቸው ዝርዝር እርምጃዎች ጋር ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤

ለ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት ወይም የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የፋይናንስ አቋሙን ለማስተካከል ምንም ዓይነት ወይም በቂ የሆኑ እርምጃዎች አልተወሰዱም የሚል አስተያየት ካለው በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት የቦርድ አባላት እንዲተኩ እና አዲስ የቦርድ አባላት እንዲሾሙ ለሆልዲንግ ኩባንያው ወይም አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን መመሪያ ይሰጣል።

2/ If the State-owned enterprise presents a high risk of financial distress or it is already financially distressed, the Ministry may:

a) issue a notice in writing to the State holding company or the relevant supervising authority with the assessment and detailed actions which shall be taken up by the State-owned enterprise and the State holding company or the relevant supervising authority to remedy the financial position within a specified time set by the Ministry.

b) in the event that a State-owned enterprise or the State holding company or the relevant Supervising Authority has, in its opinion, taken no or inadequate steps to rectify the State-owned enterprise's financial position within the stated deadline, issue a notice to the State holding company or the relevant supervising authority recommending the replacement of the board of members of the State-owned enterprise and directing the appointment of new board members by the state holding company or supervising authority.

www.abyssinialaw.com

ክፍል ሰባት

በመንግሥት ባለቤትነት ስለተያዘ የልማት ድርጅት ካፒታል

፳፫. በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘን የልማት ድርጅት ካፒታል ስለማቋቋም

፩/ የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በመንግሥት ባለቤትነት የሚያዝ የልማት ድርጅትን ለማቋቋም የሚስፈልገውን መነሻ ካፒታል እንዲመደብ ያደርጋል፡፡

፪/ ካፒታሉ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት ሊከፈል ይችላል፡፡ በዓይነት የሚከፈል ከሆነ የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፫)(ለ) ወይም በሚጣብ መዝገቡ መሠረት ንብረቱ በባለሙያዎች በትክክል መገመቱን ያረጋግጣል፡፡

፫/ የንግድ ሕግ አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት በሚቋቋምበት ጊዜ የሚኖረው የተከፈለ የካፒታል መጠን ከተፈቀደው ካፒታል ከ፳፭ በመቶ ያነሰ መሆን የለበትም፡፡

፬/ የተፈቀደውን ካፒታል ፳፭ በመቶ በመክፈል የተቋቋመ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት የተፈቀደውን ካፒታል ድርጅቱ ከተቋቋመበት ቀን ጀምሮ በአምስት ዓመት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ መከፈል ይኖርበታል፡፡

PART SEVEN

CAPITAL OF STATE-OWNED ENTERPRISE

23. Establishing Capital of a State-owned Enterprise

1/ A State holding company or the relevant supervising authority shall cause the initial capital needed to establish the State-owned enterprise to be allocated.

2/ The capital may be paid in cash or in kind. Where it is paid in kind, the State holding company or the relevant supervising authority shall ensure that the property is correctly valued by experts in accordance with Sub-Article (3) paragraph (b) of Article 5 of this Proclamation or in conformity with the book value thereof.

3/ Subject to the relevant provisions of the Commercial Code, the amount of the paid-up capital of a State-owned enterprise at the time of its establishment shall not be less than 25 percent of its authorized capital.

4/ The authorized capital of a State-owned enterprise permitted to be established upon the payment of 25 percent of the authorized capital shall be fully paid up within five years from the date of its establishment.

www.abyssinialaw.com

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፬) በተመለከተው መሠረት የተፈቀደው ካፒታል ሙሉ ለሙሉ ያልተከፈለ እንደሆነ የሦስተኛ ወገኖች መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የተፈቀደውን ካፒታል ከተከፈለው ካፒታል መጠን እኩል በማድረግ ያስተካክለዋል፡፡

፳፬. <u>የተፈቀደ ካፒታል መጨመር ወይም መቀነስ</u>

፩/ የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ በባለቤትነቱ ሥር ያለውን በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትን ካፒታል ለማሳደግ የሚያስፈልገውን ገንዘብ በመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ያስመድባል ወይም በመንግሥት ባለቤትነት ከተያዘው የልማት ድርጅት የተጣራ ትርፍ እንዲከፈል ያደርጋል፡፡

፪/ ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ካፒታልን ለመጨመር የሚያስፈልገው ገንዘብ በመንግሥት እንዲመደብ ወይም በመንግሥት ባለቤትነት ከተያዘ የልማት ድርጅት የተጣራ ትርፍ እንዲከፈል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የውሳኔ ሀሣብ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፫/ ሦስተኛ ወገኖች ያላቸው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት የተፈቀደ ካፒታል የሚቀነሰው፤

ሀ) ኦዲተሮች የተፈቀደው ካፒታል እንዲቀንስ ሀሣብ ሲያቀርቡ፤

5/ Where the authorized capital is not fully paid-up as provided under Sub-Article (4) of this Article, the State holding company or the relevant supervising authority without prejudice to the rights of third parties, adjust the capital to the level of the paid-up capital.

24. <u>Increase or Decrease of Authorized Capital</u>

1/ A State holding company may cause the funds needed to increase the capital of a State- owned enterprise under its ownership to be allocated by the State holding company or to be paid out of the net profits of the State-owned enterprise.

2/ A supervising authority may recommend to the Council of Ministers the funds needed to increase the capital of a State-owned enterprise under its portfolio to be allocated by the Government or to be paid out of the net profits of the State-owned enterprise.

3/ The authorized capital of a State-owned enterprise may, without prejudice to the rights of third parties, be decreased where:

a) the auditors have proposed that the authorized capital should be decreased;

www.abyssinialaw.com

ለ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት የዳይሬክተሮች ቦርድ የቀረበ ሀሣብን ተከትሎ የተፈቀደው ካፒታል እንዲቀንስ ከተወሰነ፤ እና

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተፈቀደው ካፒታል ሙሉ ለሙሉ ካልተከፈለ፤ ነው።

b) it is decided to decrease the authorized capital following a proposal by the board of directors of the State-owned enterprise to this effect; and

c) the authorized capital of the enterprise has not been fully paid as provided for under Article 23 Sub-Article (4) of this Proclamation.

ክፍል ስምንት

በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ስም እና የንግድ ስም

፳፭. በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ስም

፩/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ስም የሚያከናውነውን ሥራ የሚገልፅ ስም ሆኖ ስሙም ሥራውን በግልጽ የሚያመለክት መሆን ይኖርበታል።

፪/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ስም የመንግሥት ፖሊሲንና ሞራልን የሚቃረን እና የሦስተኛ ወገኖችን መብት የሚነካ መሆን የለበትም።

፫/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ስም በማንኛውም የመንግሥት ወይም የግል ድርጅት ያልተመዘገበ መሆን አለበት።

፬/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ስሙን ሥራውን በሚያከናውንበት ቦታ በግልፅ እንዲታይ ማድረግ ይኖርበታል።

PART EIGHT

NAME OF A STATE-OWNED ENTERPRISE AND TRADEMARK

25. Name of State-owned Enterprise

1/ The name of a State-owned enterprise is the name under which the State-owned enterprise carries on its activities, and it shall clearly designate such activities.

2/ The name of a State-owned enterprise shall not offend public policy and moral and it shall not prejudice the rights of third parties.

3/ The name of a State-owned enterprise shall be available for use and not formed or registered under another State-owned or private enterprise.

4/ A State-owned enterprise shall display its name in a clearly visible manner in the premises where it conducts its business.

www.abyssinialaw.com

፳፮. የንግድ ምልክት

፩/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ማናቸውንም ንግድ ምልክት ሊጠቀም ይችላል፡፡

፪/ የንግድ ምልክት ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት አግባብ ባለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት መመዝገብና ሀገር ዐቀፍ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ መውጣት ይኖርበታል፡፡

ክፍል ዘጠኝ
በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ሂሣብ እና የኦዲት ምርመራ

፳፯. የሂሣብ አያያዝ መርሆዎች

፩/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬፻፵፯/፪ሺ፮ መሠረት ዓለም ዐቀፍ የሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎችን በመከተል የሂሣብ መዝገብ መያዝ እና የፋይናንስ ሪፖርቶች ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

፪/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት እና እያንዳንዱ ተቀጥላ ድርጅቱ፤

ሀ) ግብይቶችን፣ የፋይናንስ አቋምንና የሥራ አፈፃፀምን በትክክል የሚመዘግብበትና የሚያስረዳ፤

ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት የሂሣብ መግለጫዎች ለማዘጋጀትና የኦዲት ሥራ ለማከናወን የሚያስችል፤

26. Trademark

1/ A State-owned enterprise may use any trademark in accordance with the applicable law.

2/ Before a trademark is used, it shall be registered by the appropriate government office and published in a newspaper of nation wide circulation.

PART NINE
ACCOUNTS AND AUDITING OF ACCOUNTS OF STATE-OWNED ENTERPRISES

27. Accounting Principles

1/ A State-owned enterprise shall keep books of accounts and prepare financial reports following International Financial Reporting Standards as per the Financial Reporting Proclamation No. 847/2014.

2/ A State-owned enterprise and each of its subsidiaries shall keep written financial records that:

a) correctly record and explain its transactions and financial position and performance;

b) will enable financial statements to be prepared and audited in accordance with this Proclamation;

www.abyssinialaw.com

ሐ) በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሕጎች የሚጠየቁትን የፋይናንስ ሪፖርቶች ለማዘጋጀት የሚያስችል በጽሑፍ የሰፈረ የፋይናንስ መረጃዎችን ይይዛል፡፡

c) will enable other financial reports required by this Proclamation and other relevant laws to be prepared.

፳፰. <u>የበጀት ዓመት</u>

፩/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት የበጀት ዓመት በኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር ሐምሌ ፩ ጀምሮ ሰኔ ፴ የሚያበቃው የኢትዮጵያ የበጀት ዓመት ይሆናል፡፡

፪/ ሆኖም በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት ቀደም ሲል ከኢትዮጵያ ውጭ ባከናወነው ሥራ ምክንያት የበጀት ዓመቱን በኢትዮጵያ ቀን አቆጣጠር ማድረግ ያልቻለ እንደሆነ በባለቤትነት በያዘው የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ባለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ፈቃድ የተለየ የበጀት ዓመት መጠቀም ይችላል፡፡

28. <u>Financial Year</u>

1/ The financial year of a State-owned enterprise shall be the Ethiopian fiscal year that begins on Hamle 1 and ends on Sene 30 of the Ethiopian Calendar.

2/ If the State-owned enterprise is unable to use the financial year in accordance with the Ethiopian calendar due to previous performance or work outside of Ethiopia, it may use a different financial year with the permission of the State holding company it is owned by or the relevant supervising authority.

፳፱. <u>ኦዲተሮችን ስለመሾም</u>

፩/ በሕግ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር ወይም በእርሱ ለተሰየመ ኦዲተር የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው፣ የእያንዳንዱ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ሂሣብ በመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብነት ባለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በተሾመ ገለልተኛ የውጭ ኦዲተሮች ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን በመከተል ይመረመራል፡፡

፪/ ቦርዱ በመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ባለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ፈቃድ የውጭ ኦዲተሮችን የሥራ ዘመንና ክፍያ ይወስናል፡፡

29. <u>Appointment of Auditors</u>

1/ Without prejudice to the powers and duties of the Federal Auditor General or its designee auditor under other laws, the accounts of each State-owned enterprise shall be audited by independent external auditors appointed by the State holding company or the relevant supervising authority according to International Standards on Auditing.

2/ The board, with the consent of the State holding company or the relevant supervising authority shall determine the term and payment of the external auditors.

www.abyssinialaw.com

፫/ የፋይናስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፯/፪ሺ፮ የኦዲተሮችን ሥልጣን፣ ተግባራትና ተጠያቂነት በተመለከተ እንደአግባቡ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

3/ The Financial Reporting Proclamation No. 847/2014 shall apply, mutatis mutandis, with respect to the powers duties and liability of auditors.

፴. ሪፖርት ስለማቅረብና መረጃን ስለመግለጽ

፩/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ሂሣቡን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መዝጋት ይኖርበታል። የዓመቱ የሂሣብ መዝጋት ሥራ የበጀት ዓመቱ ባበቃ ከሦስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን መቅረብ ይኖርበታል።

30. Reporting and Disclosure

1/ A State-owned enterprise shall close its accounts at least once a year. The annual closing of accounts shall be completed not later than three months after the end of a financial year and the report shall be submitted to a State holding company or the relevant supervising authority.

፪/ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፯/፪ሺ፮ እንደአግባቡ በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ፣ በኦዲት ሥራና በመረጃ መግለጽ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

2/ The Financial Reporting Proclamation No. 847/2014 shall apply, mutatis mutandis, with respect financial reporting, auditing and disclosure.

፫/ ዓመታዊ ሪፖርቱ፤

3/ The annual report shall:

ሀ) በዚህ አዋጅ የሚጠየቅ ከበጀት ዓመቱ ጋር የተያያዘ በኦዲተር የተመረመረ የፋይናንስ መግለጫዎችን ማካተት ይኖርበታል፤

a) include the audited financial statements required by this Proclamation for the financial year to which it relates;

ለ) የፋይናንስ መግለጫዎቹን የሚመለከት የኦዲተር ሪፖርትን ማካተት ይኖርበታል፤

b) include the report of the auditor for those financial statements;

ሐ) ከሪፖርቱ ጋር ተያያዥ በሆነው የበጀት ዓመት ውስጥ በመንግሥት ባለቤትነት በተያዘ የልማት ድርጅት የተከናወነው ሥራ ለተጠቀሰው ዓመት በንግድ ዕቅዱ ከተቀመጠው ግቦች ወይም የሥራ መለኪያዎች አንፃር መገምገም ይኖርበታል።

c) compare the actual performance of the State-owned enterprise during the financial year to which the report relates with the targets set in its business plan for that financial year.

www.abyssinialaw.com

፬/ የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት ዓመታዊ ሪፖርት እንደደረሰው ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የፊስካል ስጋት ክትትልና ግምገማ ለማካሄድ እንዲያስችለው ሪፖርቱ እንዲደርሰው ማድረግ ይኖርበታል፡፡

4/ A State holding company or the relevant supervising authority shall forward to the Ministry a copy of State-owned enterprises' annual report upon receipt to enable fiscal risk monitoring and analysis of the Ministry laid down under Article 22 Sub-Article (1) of this Proclamation.

፭/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ሪፖርቱን ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ባቀረበ በአንድ ወር ውስጥ ሙሉ ዓመታዊ ሪፖርቱን በኦዲተር ከተመረመረው የፋይናንስ መግለጫዎች ጋር ለሕዝቡ ሊደርስ በሚችል የማስተላለፊያ ዘዴ እና በራሱ ድኅረ ገጽ ማውጣት ይኖርበታል፡፡

5/ A State-owned enterprise shall arrange for the publication of the full annual report together with audited financial statements on a medium where the public will have access and on the website maintained by the State-owned enterprise within one month after the report is submitted to the State holding company or the relevant supervising authority.

፮/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት የበጀት ዓመቱን የሩብ እና የመንፈቅ ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ዓመቱ፣ የሩብ ወይም የመንፈቅ ዓመቱ ባበቃ በሁለት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብነት ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

6/ A State-owned enterprise shall submit to the State holding company or the relevant supervising authority a quarterly, semi-annual and annual report of the operations of the State-owned enterprise for the period to which it relates no later than two months after the end of the period.

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) የተመለከተው የሩብ ዓመት፣ የመንፈቅና የዓመት ሪፖርቶች፣

7/ The quarterly, semi-annual and annual reports mentioned in Sub-Article (6) of this Article shall:

ሀ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት ወይም በስሩ ያሉ ተቀጥላ ድርጅቶች በበጀት ዓመቱ የንግድ ዕቅድ ከቦርዱ ጋር በስምምነት ያስቀመጧቸውን ግቦች ምን ያህሉን እንዳከናወኑ መግለጽ ይኖርበታል፣ እና

a) state to what extent the State-owned enterprise and, if any, its subsidiaries have achieved the business goals specified in its business plan for the financial year; and

www.abyssinialaw.com

ለ) የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት እንዲያካትታቸው መመሪያ የተሰጠበትን ሌሎች ጉዳዮችን ማካተት አለበት፡፡

፴፩. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

በኦዲት ምርመራ ያለን በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትን ገንዘብ የተቀበለ፣ የከፈለ ወይም ወጪ ያደረገ ወይም የድርጅቱ ንብረት በኃላፊነቱ ሥር ያለ ማናቸውም ሰው ሲጠየቅ ሊመረመር የሚገባውን ሂሣብና አስፈላጊ መረጃዎች ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

<u>ክፍል አሥር</u>
<u>የመጠባበቂያ ገንዘብና ታክስ</u>

፴፪. <u>ስለመጠባበቂያ ገንዘብና አጠቃቀሙ</u>

፩/ እያንዳንዱ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) በተመለከተው መሠረት ሕጋዊ የመጠባበቂያ ገንዘብ ማቋቋምና መያዝ ይኖርበታል፡፡

፪/ በሌሎች ሕጎች በተለየ መልኩ የተደነገጉ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ እያንዳንዱ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት የካፒታሉን ሃያ በመቶ እስኪደርስ ድረስ በየዓመቱ ከሚያገኘው የተጣራ ትርፍ አምስት በመቶ ወደ ሕጋዊ መጠባበቂያ ገንዘብ ማስገባት አለበት፡፡

፫/ ሕጋዊ መጠባበቂያ ገንዘቡ ኪሣራን፣ ያልታሰቡ ወጪዎችንና ዕዳዎችን ለመሸፈን ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

b) include any other matter that the State holding company or the relevant supervising authority has directed the State-owned enterprise to include.

31. <u>Obligation to Cooperate</u>

Any person who has received, paid or expended money, or is in charge of the accounts of, the money or property of the State-owned enterprise being audited shall, when requested, have the obligation to produce to the auditors the accounts to be audited and to furnish the necessary information.

<u>PART TEN</u>
<u>RESERVE FUND AND TAXES</u>

32. <u>Reserve Funds and their Utilization</u>

1/ Every State-owned enterprise shall establish and maintain a legal reserve fund as described in Sub-Article (2) and (3) of this Article.

2/ Without prejudice to the provisions of other laws providing otherwise, every State-owned enterprise shall annually transfer 5 percent of its net profits to the legal reserve fund until such reserve fund equals 20 percent of the capital of the State-owned enterprise.

3/ The legal reserve fund may be utilized for covering losses and unforeseeable expenses and liabilities.

www.abyssinialaw.com

፴፪. ግብር፣ ታክስና ቀረጥ ስለመክፈል

፩/ ግብር፣ ታክስንና ቀረጥን የሚመለከቱ አግባብነት ያላቸው ሕጎች በመንግሥት ባለቤትነት በተያዙ የልማት ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች በሌሎች ሕጎች ከግብር፣ ከታክስና ከቀረጥ ነፃ የመሆንን እና ሌሎች መብቶችን የሚያስቀር አይሆንም፡፡

32.Payment of Taxes and Duties

1/ The relevant laws concerning taxes and duties shall be applicable to State-owned enterprises.

2/ Without prejudice to the provisions of Article 10 of this Proclamation, any other provisions of this Proclamation shall not affect the right of a State-owned enterprise to be exempt from taxes and duties and any other right under any other law.

፴፬. የትርፍ ድርሻ ስለመክፈል

የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ ፲፮ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የትርፍ ድርሻ የበጀት ዓመቱ ባበቃ በአራት ወራት ውስጥ እንደ አግባብነቱ ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም ለሚኒስቴሩ መከፈል ይኖርበታል፡፡

34. Payment of State Dvided

Subject to Article 13 Sub-Article (16) of this Proclamation, State holding companies and State-owned enterprises under the oversight of supervising authorities shall pay dividend to the Ministry within four months following the end of the financial year.

ክፍል አሥራ አንድ
በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ውህደት፣ መከፈል

PART ELEVEN
MERGER AND DIVISION OF A STATE-OWNED ENTERPRISE

፴፭. ስለውህደትና መከፈል

፩/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ሌላ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የልማት ድርጅቶችን በመጠቅለል ወይም አብሮ በመዋሃድ አዲስ ድርጅት በመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ውሳኔ ወይም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ማቋቋም ይችላል፡፡

35. Merger and Division

1/ A State-owned enterprise may be merged either by taking over one or more State-owned enterprises or by the formation of a new State-owned enterprise by the decision of a State holding company or the Council of Ministers.

www.abyssinialaw.com

፪/ አንድ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትን ለሁለት ወይም ከሁለት በላይ በመከፈል ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የልማት ድርጅቶች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ሊቋቋም ይችላል፡፡

፫/ አንድ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ለሁለት ወይም ከሁለት በላይ ከመከፈሉ ወይም ከመቀላቀሉ በፊት ሂሳቡ አዲት መደረግ ይኖርበታል፡፡

፴፮. <u>የተዋሃደ ወይም የተከፈለ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት መብትና ግዴታዎች ስለማስተላለፍ</u>

፩/ በውህደት ምክንያት ህልውናውን ያጣ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት መብትና ግዴታዎች ለጠቀለለው በመንግሥት ባለቤትነት ለተያዘ የልማት ድርጅት ወይም በውህደት ለተፈጠረው አዲስ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ሊተላለፍ ይችላል፡፡

፪/ የሚከፈል በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት መብትና ግዴታዎች ለተከፈሉት የልማት ድርጅቶች ስለሚመደቡበት ሁኔታ በመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ይወሰናል፡፡

፫/ የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የመከፈሉን ውሳኔ እና መብትና ግዴታዎች ለተከፈሉት በመንግሥት ባለቤትነት ለተያዙ የልማት ድርጅቶች የሚከፋፈሉበትን መግለጫ የያዘ የተሟላ ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡

2/ A State-owned enterprise may be divided to form two or more new State-owned enterprises by the decision of the Council of Ministers.

3/ The accounts of a State-owned enterprise to be merged or divided shall be audited before the merger or division takes effect.

36. <u>Transfer of Rights and Obligations of a State-owned Enterprise Merged or Divided</u>

1/ The rights and obligations of a State-owned enterprise that ceases to exist as a result of merger shall be transferred to the State-owned enterprise taking over or to the new State- owned enterprise resulting from the merger or to a State holding company.

2/ The distribution of the rights and obligations of a State-owned enterprise being divided shall be determined by a State holding company or the Council of Ministers.

3/ A State holding company or the relevant supervising authority shall prepare a complete report containing the decision to divide and a statement as to the distribution of rights and obligations to the State-owned enterprises resulting from the division.

www.abyssinialaw.com

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌዎች ቢኖሩም፣በመከፈል የተፈጠረው እያንዳንዱ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅት በመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ባለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በተመደበላቸው የዕዳ መጠን ከመከፈሉ በፊት ለነበረው በመንግሥት ባለቤትነት ለተያዘ የልማት ድርጅት ገንዘብ ጠያቂዎች እንደአግባቡ ተጠያቂዎች ይሆናሉ።

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) of this Article, the State-owned enterprises resulting from the division shall be liable towards the creditors of the State-owned enterprise divided for the portion of debt allocated to them by a State holding company or the Council of Ministers.

ክፍል አሥራ ሁለት
በመንግሥት ባለቤትነት ስለተያዘ የልማት ድርጅት መፍረስና ንብረት ማጣራት

PART TWELVE
DISSOLUTION AND WINDING-UP OF STATE-OWNED ENTERPRISES

፴፯. የመፍረሻ ምክንያቶች

በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊፈርስ ይችላል፣

፩/ የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም የሚኒስትሮች ምክር ቤት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትን ህልውና የሚነካ ውሳኔ ካስተላለፈ፣

፪/ በማቋቋሚያ ደንቡ ወይም በመመሥረቻ ጽሑፍ በተወሰነው መሠረት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት የመቆያው ጊዜ ሲያበቃ፣

፫/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት የተቋቋመበትን ሥራዎች ሲያጠናቅቅ፣

፬/ በማቋቋሚያ ደንቡ ወይም በመመሥረቻ ጽሑፉ የተደነገጉት ዓላማዎች የማይሳኩ ወይም የማይፈፀሙ ሲሆን፣

37. Grounds for Dissolution

A State-owned enterprise may be dissolved by any one of the following reasons:

1/ A decision of a State holding company or the Council of Ministers affecting the existence of the State-owned enterprise;

2/ The expiry of the life of the State-owned enterprise as fixed in its establishment Regulation or Memorandum of Association;

3/ Completion of the venture for which the State-owned enterprise was established;

4/ Failure of the purpose or impossibility of performance as determined in its establishment Regulation or Memorandum of Association;

www.abyssinialaw.com

፫/ በመንግሥት ባለቤትነት ከተያዘው የልማት ድርጅት የተከፈለው ካፒታል ውስጥ ፸፭ በመቶ የሚሆነውን ሲያጣ፤ እና

፮/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት በሕግ ሥልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት ውሳኔ መክሰሩ ሲታወጅ፡፡

፴፰. ስለመክሰርና ሂሣብ ማጣራት

፩/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትን ኪሳራ እና ተያያዥ የንብረት ማጣራትን በተመለከተ የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች እንደ አግባቡ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፪/ በንግድ ሕግ የተደነገገው ቢኖርም በሕግ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት ኪሳራ አወሳሰን ሂደት በተፋጠነ ሥርዓት እንዲከናወን ሊወስን ይችላል፡፡

፴፱. ስለንብረት አጣሪዎች ሹመት፣ ተግባራትና ሥልጣን

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፰ እንደተመለከተው የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የኢትዮጵያ ሂሣብ አያያዝና አዲት ቦርድ ያወጣው መስፈርቶች የሚያሟላ እና በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ሠራተኞች ያልሆኑ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ንብረት አጣሪዎችን ሊሾም ይችላል፡፡

፪/ የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በበቂ ምክንያት ንብረት አጣሪዎችን በማሰናበት በአዲስ ንብረት አጣሪዎች ሊተካቸው ይችላል፡፡

5/ Loss of 75 percent of the paid-up capital of the State-owned enterprise; and

6/ Decision by a competent court declaring the State-owned enterprise bankrupt.

38. Bankruptcy and Winding-up

1/ The provisions of the Commercial Code shall apply, mutatis mutandis, to the bankruptcy, winding-up and dissolution of a State-owned enterprise.

2/ Notwithstanding the provisions of the Commercial Code, a competent court of law may decide that bankruptcy proceedings of a State-owned enterprise be conducted by way of summary procedure.

39. Appointment, Duties and Powers of Liquidators

1/ In cases referred to under Article 38 of this Proclamation, the State holding company or the relevant supervising authority shall appoint one or more liquidators that could satisfy the criteria set by the Accounting and Auditing Board of Ethiopia and who are not employees of the State-owned enterprise.

2/ The State holding company or the relevant supervising authority may dismiss the liquidators and replace them with other liquidators for good cause.

www.abyssinialaw.com

፫/ ንብረት አጣሪዎች በመጣራት ላይ ያለውን በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትን የሂሣብ ደብተርና ሰነዶች በይዞታቸው ሥር ያደርጋሉ፡፡

4/ Unless the State holding company or the relevant supervising authority decides otherwise, the liquidators shall take possession of the property of the State-owned enterprise.

፬/ የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር፣ ንብረት አጣሪው በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትን በይዞታው ሥር ያደርጋል፡፡

5/ Unless the State holding company or the relevant supervising authority decides otherwise, the liquidators shall assume the powers and duties of the board and the chief executive officer of the State-owned enterprise.

፭/ የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር፣ ንብረት አጣሪው በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ቦርድና የዋና ሥራ አስፈፃሚው ሥልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡፡

6/ Without prejudice to the provision of Sub-Article (4) of this Article, the liquidators may not undertake new business unless required for the execution of contracts still running or where the interests of the winding-up so require.

፮/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ንብረት አጣሪዎቹ በሂደት ላይ ያሉ ውሎችን ለማስፈፀም ወይም ለንብረት ማጣራቱ ጥቅሞች አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር አዲስ ሥራ መጀመር አይችሉም፡፡

7/ The board shall prepare a report for the liquidators on the financial standing of the State- owned enterprise.

፯/ ቦርዱ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት የፋይናንስ አቋም በተመለከተ ለንብረት አጣሪዎች ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡

8/ The liquidators and the board shall jointly prepare and sign a statement of financial standing summarizing the rights and obligations of the State-owned enterprise.

፰/ ንብረት አጣሪዎችና ቦርዱ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት መብቶችና ግዴታዎች በአጭሩ የያዘ የፋይናንስ አቋም መግለጫ በጋራ በማዘጋጀት ይፈርሙበታል፡፡

www.abyssinialaw.com

፱/ በመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያ ወይም አግባብ ባለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚ ንብረት አጣሪዎቹ ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት እገዛ ያደርጉላቸዋል፡፡

9/ Unless the State holding company or the relevant supervising authority decides otherwise, the board and the chief executive officer of the State-owned enterprise shall assist the liquidators in carrying out their duties.

፵. ገንዘብ ጠያቂዎችን ስለመጥራት

40. Calling on Creditors

፩/ ንብረት አጣሪዎች በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት የሚፈርስ መሆኑን በማሳወቅ ያላቸውን የገንዘብ ጥያቄ በማስረጃ በማስደገፍ እንዲያቀርቡ ለገንዘብ ጠያቂዎች ያስታውቃሉ፡፡

1/ The liquidators shall inform creditors of the proposed dissolution of the State-owned enterprise and require them to file their claims with supporting documents.

፪/ ስማቸው በመንግሥት ባለቤትነት በተያዘው የልማት ድርጅት መዝገብ ተመዝግቦ ለሚገኙ እና በሌላ ሁኔታ ለታወቁ ገንዘብ ጠያቂዎች የድርጅቱን መፍረስ በተመዘገበ ደብዳቤ እንዲያወቁ ይደረጋል፡፡ ሌሎች በድርጅቱ ያልተመዘገቡ ገንዘብ ጠያቂዎች በሀገር ዐቀፍ ደረጃ በሚሰራጭ ጋዜጣ በየሳምንቱ በሚወጡ ሶስት ተከታታይ ማስታወቂያዎች እንዲያውቁ ይደረጋል፡፡

2/ Creditors appearing in the books of the State-owned enterprise or who are otherwise known shall be notified of the proposed dissolution by a registered letter. Other creditors who are unknown shall be notified by notice published in three successive weekly issues of a newspaper of nationwide circulation.

፫/ ገንዘብ ጠያቂዎች ያሏቸውን የገንዘብ ጥያቄዎቻቸውን ደብዳቤ ከደረሳቸው ወይም የመጨረሻው የጋዜጣ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በዘጠና የሥራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለባቸው፡፡

3/ Creditors shall be required to submit their claims within Ninety business days from the date of receipt of the letter or from the date of the last issue of the notice in the newspaper, as the case may be.

፬/ ንብረት አጣሪዎች በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት የፋይናንስ መግለጫ ከውሳኔ ሃሣቦች፣ ከገንዘብ ጠያቂዎች ዝርዝርና ክፍያ ከሚፈፀምበት ቅደም ተከተል ጋር በማዘጋጀት ለመንግሥት ሆልዲንግ

4/ The liquidators shall be required to prepare and submit to the State holding company or the relevant supervising authority a financial statement of the State-owned

www.abyssinialaw.com

ኩባንያው ወይም አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ማቅረብ አለባቸው፡፡

enterprise together with their recommendations and a list of creditors and priorities, according to which such payments are to be made.

፭/ የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የንብረት አጣሪዎች ያዘጋጁትን የሂሣብ መግለጫ መሠረት በማድረግና ያቀረቡትን ሀሣብ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣

5/ The State holding company or the relevant supervising authority shall, on the basis of the financial statement prepared by the liquidators and after taking into consideration their recommendations:

ሀ) የገንዘብ ጥያቄያቸውን በማስረጃ በማስደገፍ ላቀረቡ ገንዘብ ጠያቂዎች ክፍያው እንዲፈፀም ይፈቅዳል፡፡

a) authorize the payment of creditors who have filed their claims with the necessary proof;

ለ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት ጥሬ ገንዘብ ለገንዘብ ጠያቂዎች መክፈል ያለበት ዕዳ የማይሸፍን ሆኖ ሲገኝ የሶስተኛ ወገኖችን መብት በማይነካ ሁኔታ የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በሚያፀድቀው የሽያጭ ዘዴ አማካይነት የልማት ድርጅቱን ንብረቶች ንብረት አጣሪዎች እንዲሸጡ ይፈቅዳል፡፡

b) where the cash balances of the State-owned enterprises are insufficient to cover the debts due to the creditors, authorize the liquidators to sell assets of the State-owned enterprise by using methods approved by the State holding company or the relevant supervising authority without affecting the rights of third parties.

ሐ) በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት ጠቅላላ ንብረት ዕዳውን ለመክፈል በቂ በማይሆንበት ጊዜና የተፈቀደው ካፒታል በሙሉ ካልተከፈለ ንብረት አጣሪዎች ቀሪው ሂሳብ በሙሉ እንዲከፈል የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያውን ወይም አግባብ ያለውን ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይጠይቃሉ፡፡

c) where the total assets of the State-owned enterprises are insufficient to cover the debts and the approved capital has not been fully paid, the liquidators may request the State holding company or the relevant supervising authority to cover the remaining debt.

www.abyssinialaw.com

፵፩. ለገንዘብ ጠያቂዎች የሚደረግ ጥበቃ

፩/ የታወቁ ገንዘብ ጠያቂዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥያቄያቸውን ሳያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ሊከፈላቸው የሚገባ ገንዘብ በገንዘብ ጠያቂዎቹ ስም በተከፈተ የባንክ ሂሣብ ተቀማጭ ይሆናል፡፡

፪/ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት የሚመለከቱ ያልተጠናቀቁ ሥራዎችን ወይም ክርክሩ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ ለገንዘብ ጠያቂዎቹ ዋስትና ያልተሰጠባቸው ክርክር ያስነሱ ጥያቄዎችን ለመሸፈን የሚያስፈልገው ገንዘብ ለብቻው ተለይቶ ይቀመጣል፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀጽ (፫) ወይም (፬) መሠረት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ህልውናውን ካጣ በኋላ በድርጅቱ መዝገቦች የማይታወቁ ገንዘብ ጠያቂዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥያቄያቸውን ያላቀረቡት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የሆነ እንደሆነ ገንዘባቸውን የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ከሰበሰበው ትርፍ ሀብት መጠየቅ ይችላሉ፡፡ በንብረት አጣሪዎች ቸልተኝነት የሚገባቸውን ክፍያ ያላገኙ ገንዘብ ጠያቂዎች ከንብረት አጣሪዎቹ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

41. Protection of Creditors

1/ Where known creditors have failed to file their claims within the time limit specified in Article 40 Sub-Article (3) of this Proclamation, the amounts due to them shall be deposited in a bank account opened in the names of the creditors.

2/ Sums shall be set aside to meet claims in respect of undertakings of the State-owned enterprise which are not completed or disputed claims where the creditors have not been guaranteed until the dispute is settled.

3/ After the State-owned enterprise ceases to exist under Sub-Article (3) or (4) of Article 42 of this Proclamation, creditors not appearing in the books of the State-owned enterprise may claim from the surplus assets collected by the State holding company or the relevant supervising authority provided their failure to claim within the time limit specified in Sub-article (3) of Article 40 of this Proclamation was due to force majeure. Creditors may claim against the liquidators, where they have not been paid owing to the liquidators' negligence.

www.abyssinialaw.com

፵፪. የመጨረሻ የሀብትና ዕዳ መግለጫ እና የመፍረስ ማስታወቂያ ስለማውጣት

፩/ ለገንዘብ ጠያቂዎች ክፍያ ከተፈፀመና በዚህ አዋጅ አንቀጽ አንቀጽ ፵፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት ሊቀርቡ የሚችሉ የገንዘብ ጥያቄዎችን ለመሸፈን የሚያስፈልገው ገንዘብ ተቀማጭ ከሆነ በኋላ ንብረት አጣሪዎች ድርጅቱ ትርፍ ሀብት ካለው ይህንኑ የሚያሳይ የመጨረሻ የሀብትና የዕዳ መግለጫ አዘጋጅተው ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በማቅረብ ለዋናው ኦዲተር በግልባጭ ያሳውቃሉ።

፪/ ዋናው ኦዲተር የሚሰጠው አስተያየት ካለው ወዲያውኑ ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ይልካል።

፫/ በመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ባለቤትነት ሥር ያለ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት የሚፈርስ ከሆነ የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው የንግድ ሕጉን ወይም አግባብነት ያለውን ሕግ ተከትሎ ድርጅቱ እንዲፈርስ ያደርጋል።

፬/ በተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሥር ያለ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት የሚፈርስ ከሆነ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ የሀብትና ዕዳ መግለጫውን እንዳፀደቀ ወዲያውኑ የንብረት ማጣራቱ ሥራ መጠናቀቁን ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያስታውቃል። የሚኒስትሮች ምክር ቤት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ ይሽረዋል። በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት

42. Final Balance Sheet and Publication of Notice of Dissolution

1/ After the creditors have been paid or sums have been set aside to meet potential claims pursuant to Article 41 Sub-articles (1) and (2), the liquidators shall prepare a final balance sheet showing surplus assets, if any, and submit the same to the State holding company or the relevant supervising authority with a copy to the Auditor General.

2/ The Auditor General shall promptly forward his comments, if any, to the State holding company or the relevant supervising authority.

3/ In the case of the dissolution of a State-owned enterprise under the ownership of a State holding company, the State holding company shall dissolve the State-owned enterprise in accordance with the Commercial Code or other applicable law.

4/ In the case of the dissolution of a State-owned enterprise under the oversight of a supervising authority, the supervising authority shall notify the Council of Ministers of the finalization of the liquidation process as soon as it approves the final balance sheet. The Council of Ministers shall then repeal the establishment regulation

www.abyssinialaw.com

ድርጅት ማቋቋሚያ ደንቡ ከተሻረበት ቀን ጀምሮ ሀልውናውን ያጣል፡፡

፭/ የፈረሰው በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው የልማት ድርጅት መዝገቦች በመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም በተቆጣጣሪው ባለሥልጣኑ ዘንድ ለ፲ ዓመት ይቀመጣል፡፡ በጉዳዩ ጥቅም ያለው ማንኛውም ሰው ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል መዝገቦቹን መመርመር ይችላል፡፡

፵፫. <u>ተራፊ ሀብት</u>

ከፈረሰና ንብረቱ ከተጣራ በመንግሥት ባለቤትነት ከተያዘው የልማት ድርጅት የተረፈ ሀብት እንደአግባብነቱ ለመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ለሚኒስቴሩ ይተላለፋል፡፡

<u>ክፍል አሥራ ሦስት</u>
<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፵፬. <u>ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስሌላቸው ሕጎች</u>

፩/ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፺፭/፲፱፻፹፬ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም የአሠራር ልምድ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፵፭. <u>የሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነት</u>

በዚህ አዋጅ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር፣ የፍትሐብሔር ሕግ፣ የንግድ ሕግ፣ የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ እና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች በመንግሥት ባለቤትነት በተያዘ የልማት ድርጅት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

of the State-owned enterprise. The State-owned enterprise shall then cease to exist.

5/ The books of the dissolved State-owned enterprise shall be deposited with the State holding company or the relevant supervising authority where they shall be kept for 10 years. Any interested person may inspect such books after payment of the prescribed fee.

43. <u>Surplus Assets</u>

Any surplus assets of a State-owned enterprise dissolved and liquidated shall devolve to its either to a State holding Company or the Ministry, as the case may be.

<u>PART THIRTEEN</u>
<u>MISCELLANEOUS PROVISION</u>

44. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>

1/ The Public Enterprises Proclamation No. 25/1992 is hereby repealed.

2/ Any law or practice that is inconsistent with the provisions of this Proclamation shall not be applicable.

45. <u>Application of Other Laws</u>

Unless otherwise provided by this Proclamation, the provisions of the Civil Code, the Commercial Code, the Trade Competition and Consumers Protection Proclamation and any other relevant laws shall apply to State-owned enterprises.

www.abyssinialaw.com

፵፮. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፬ ንዑስ አንቀፅ (፩) ቢኖርም፣ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በመንግሥት ባለቤትነት በተያዙ የልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ ደንቦች እና እነዚህን ደንቦች መሠረት አድርገው በወጡ መመሪያዎች ያሉ መብቶች፣ ጥቅሞች እና ግዴታዎች ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል።

46. <u>Transitional Provision</u>

Notwithstanding the Provisions of Sub-Article (1) of Article 44 of this Proclamation, establishing Regulations of State-owned enterprises and the rights, entitlements and duties bestowed upon them prior to the coming into force of this Proclamation shall remain in force.

፵፯. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣ ሥልጣን</u>

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦች ማውጣት ይችላል።

፪/ ሚኒስቴሩ፣ የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም ሥልጣናቸውን በሚመለከቱ ጉዳዮች አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎች ማውጣት ይችላል።

47. <u>Power to Issue Regulations and Directives</u>

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry, a State holding company or a supervising authority may issue Directives necessary for the implementation of its powers under this Proclamation and Regulations issued under Sub-Article (1) of this Article.

፵፰. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

48. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Negarit Gazette.

አዲስ አበባ ግንቦት ፮ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

ሣህለ ወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

Done at Addis Ababa, On this 16th Day of May 2024.

SAHLE-WORK ZEWDIE

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA